ትምህርት አሥራ ሦስት

የመጀመሪያ ቀን የሁለተኛ ጢሞቴዎስ መግቢያ

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደሚካሄደው የቀብር ሥነ ሥርዓት እየሄድክ ነው እንበል፥ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ገብተህ ስትቀመጥ፥ ከቤተ ክርስቲያኒቱ መድረክ ላይ የተኛው አስከሬን ያንተው መሆኑን ትገነዘባለህ። የራስህን የቀብር ሥነ ሥርዓት እየተመለከትህ ነው እንበል። ፕሮግራሙን እየተከታተልህ እያለ፥ ከልጆችህ ታላቁ ብድግ ብሎ በልጅነቱ ከአንተ ጋር ስለነበረው ግንኙነትና ስለ አንተ የሚያስታውሳቸውን ነገሮች ለማኅበረ ምእመናኑ ይናገራል። ሁለተኛ፥ ባለቤትህም በበኩሏ ባሏ እንደ መሆንህ መጠን ስለ አንተ የምታስታውሰውን ትናገራለች። ሦስተኛ፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌም ስለ አንተ የሚያውቀውንና የሚያስታውሰውን ይናገራል። አራተኛ፥ የሥራ ባልደረባህም እንዲሁ በሥራ ቦታ ምን ዓይነት ሰው እንደነበርክ ይመሰክራል። አምስተኛ፥ የማኅበረሰብህ አባል የሆነ ሰውም እንዲሁ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የነበረህን ድርሻ ያብራራል። ስድስተኛ፥ በመንፈሳዊ ዓይንህ በክርስቶስ ፊት ቆመህ የእርሱን ግምገማ ትሰማለህ። እነዚህ ሰዎች ሁሉ እውነትን የሚናገሩ ሲሆን፥ የሚያሳዝኑህን ነገሮችንም እንዲሁ ይናገራሉ።

> ፩ኛ ጥያቄ፡- ይህን ትዕይንት በአእምሮህ ስትስል፥ ሀ) እያንዳንዱ ሰው ስለ አንተ በእውነት ምን ቢናገር ደስ ይልሃል? ለ) በቀብር ሥነ ሥርዓትህ ላይ እንዲነገሩ የምትፈልጋቸው ምስክርነቶች ስለ ባሕሪህና ስለ ተግባሮችህ አስፈላጊ ነገሮችን ይናገራሉ። ሰዎች ስለ አንተ እንዲናገሩ የምትፈልገውን ከራስህ እውነተኛ ማንነትህ ጋር አነጻጽር። በምትሞትበት ጊዜ የምትፈልገው ነገር የሆንከውን ይሆን ዘንድ ልትለውጣቸው የሚገቡህ የሕይወትህ ክፍሎች ምን ምንድን ናቸው?

መጽሐፍ ቅዱስ ሁላችንም እንደምንሞትና አንድ ቀን በክርስቶስ ፊት ቆመን ስለ ሕይወታችን የሚሰጠውን ግምገማ እንደምንከታተል ያስተምራል። ያም ግምገማ በክርስቶስ ማመን አለማመናችንን የሚመለከት አይሆንም። ሁሉም የሕይወታችን ክፍሎችና የነበሩን የግንኙነት ዓይነቶች በሙሉ ይገመገማሉ። ዛሬ በሕይወታችን አስፈላጊው ነገር ምን እንደሆነ ለይተን ካላወቅን፥ ክርስቶስ ወይም ሌሎች ሰዎች በምን ዓይነት ባሕርያት ወይም ተግባራት እንደሚያስታውሱን ካልወሰንን፥ አብዛኞቻችን በሕይወት ውስጥ ጠቃሚ በሆኑት ጉዳዮች ላይ አናተኩርም። በምንሞትበት ጊዜ፥ የቤተሰብ ውርሳችን፥ ጎላችን፥ ትምህርታችን፥ ሀብታችን፥ ወይም ኃይላችን ወሳኝ ጠቀሜታ አይኖራቸውም። ይልቁንም የተሻልን ወላጆችና አፍቃሪ የትዳር ጓደኞች መሆናችን ወሳኝነት ይኖረዋል። እውነትን የምንወድና ለሌሎች የምናስብ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ እውነተኛና ታማኝ ሠራተኞች፥ የማኅበረሰቡን ሕይወት ለማሻሻል የጣርንና ለእግዚአብሔር ክብር በታማኝነት የተመላለስን ሰዎች በሆንን ብለን እንመኛለን። እነዚህ በሰው ሕይወት ውስጥ ጉልህ ሚና ያላቸውና በክርስቶስም ፊት በምንቆምበት ጊዜ የምንገመገምባቸው ነጥቦች ናቸው (፩ኛ ቆሮ. 3፡10–15)።

በ2ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ፥ ጳውሎስ በሰማዕትነት ከማለፉ ጥቂት ቀደም ብሎ የጻፈውን የመጨረሻ ደብዳቤ እናገኛለን። ጳውሎስ ሕይወቱን መለስ ብሎ ሲመለከትና ወደፊት አሻግሮ የዘላለምን ሕይወት ሲያይ፥ ስለ ሕይወት የነበረውን አመለካከት ይገልጻል። ጳውሎስ ወደ ኋላ ከዚያ ወደፊት ሲመለከት፥ *«በመሥዋዕት እንደሚደረግ፥ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፥ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል። መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም»* ይላል (2ኛ ጢሞ. 4፡6-8)። ጳውሎስ ሊሞት ሲቃረብ ያሳለፈውን ሕይወት የተመለከተው በጸጸት ሳይሆን በእርካታ ነበር። እንዲሁም የወደፊት ሕይወቱን ክርስቶስ ምን ይለኛል በሚል ፍርሃት ሳይሆን በልበ ሙሉነት ቃኝቶታል። ይህ የሆነው ጳውሎስ ሕይወቱን ለወንጌሉ እንደሚገባ አድርጎ እንደኖረ ያውቅ ስለነበር ነው። ከሥራ ጓደኞቹ፥ ከማኅበረሰቡ ጋር የነበረው ግንኙነት ፈሪሃ እግዚአብሔር የነገሠበት ነበር። ስለሆነም በእግዚአብሔር ፊት በሚቆምበት ጊዜ እንደማያፍር ያውቅ ነበር።

2ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለአንድ ሰው በሕይወቱ መጨረሻ የኋላውን ያለ ጸጸት፥ የፊቱን ደግሞ በልበ ሙሉነት መመልከት አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) አሁን ሞተህ በእግዚአብሔር ፊት ብትቀርብ የምትጸጸትባቸው አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? በክርስቶስ ፊት ብትቆም ምንን ትፈራለህ? በምትሞትበት ጊዜ ከጸጸት ወይም ከፍርሃት ነፃ ትሆን ዘንድ ቅድሚያ በምትሰጣቸው ነገሮች፥ በባሕሪህና በተግባርህ ውስጥ ሊለወጡ የሚገባቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

የ2ኛ ጢሞቴዎስ ደራሲ

3ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ጢሞ. 1፡1 አንብብ። ሀ) የመጽሐፉ ደራሲ ማን ነው? ለ) መጽሐፉ የተጻፈው ለማን ነው? ሐ) 2ኛ ጢሞቴዎስን በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገብ ቃላት ውስጥ በመመልከት ስለ ደራሲው፥ መልእክቱን ስለሚቀበሉት ሰዎችና ስለ መጽሐፉ የተገለጸውን ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

ጳውሎስ የ2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክቱን የጀመረው እንደተለመደው ራሱን፥ *«በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነው ጳውሎስ»* በማለት ነበር። ልክ እንደ 1ኛ ጢሞቴዎስ ሁሉ፥ ጳውሎስ ይህንንም መልእክት የጻፈው ለጢሞቴዎስ የራሱን ሐዋርያዊ ሥልጣን ለማስገንዘብ ብቻ አልነበረም። ነገር ግን ጢሞቴዎስ የቤተ ክርስቲያኒቱን ተግባራት ለማከናወን በሚፍጨረጨርበት ወቅት ይህንን ደብዳቤ የሥልጣኑ መሠረት አድርጎ እንዲጠቀምበት ይፈልጋል።

መልእክቱ የተጻፈው ለማን ነበር?

ጳውሎስ በዚህ ደብዳቤ መግቢያ ውስጥ ለተወደደው ልጁ ለጢሞቴዎስ ሲል ጽፎአል። ጳውሎስ ትዳር ስላልነበረው ከአብራኩ የወጣ ልጅ አልነበረውም። ጢሞቴዎስ ግን ከ15 ዓመታት በላይ አብሮት የሠራ ከመሆኑም በላይ እንደ ልጁ የሚያየው አገልጋይ ነበር። ስለሆነም ጳውሎስ በሰማዕትነት ከማለፉ ጥቂት ቀደም ብሎ ጥልቅ ፍቅሩን የገለጸበትን

መልእክት ለጢሞቴዎስ ጽፎአል። ይህም የጳውሎስ የመጨረሻው መልእክት ነበር።

ጳውሎስ 2ኛ ጢሞቴዎስን የጻፈበት ጊዜና ስፍራ

ባለፈው ሳምንት እንደተመለከትነው፥ ምሁራን በጳውሎስ ሕይወት መጨረሻ ምን እንደ ተፈጸመ ይከራከራሉ። አንዳንዶች የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከተጻፈ በኋላ ጳውሎስ በችሎት ፊት ተመርምሮ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ በሮም ውስጥ እንደ ተገደለ ያስባሉ። ይህ እውነት ከሆነ 2ኛው የጢሞቴዎስ መልእክት የተጻፈው ከ63–65 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ መሆኑ ነው። ይህም በሐዋርያት ሥራ ታሪክ መጨረሻ ላይ ጳውሎስ ሊሞት ጥቂት ወራት ሲቀሩት የተጻፈው መሆኑን ያሳያል።

ይሁንና ጳውሎስ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከተጻፈ በኋላ ከእስር ቤት የተፈታ ይመስላል። ከዚያ በኋላ ለቀጣይ አያሌ ዓመታት በምዕራባዊ የሮም ግዛት (ስፔን) ካገለገለ በኋላ ወደ ምሥራቅ ትንሹ እስያና ግሪክ የተጓዘ ይመስላል። በ66 ዓ.ም አካባቢ ጳውሎስ እንደገና ታስሮ ወደ ሮም ተወሰደ። ጳውሎስ ልብሶቹንና መጽሐፎቹን ለመያዝ ጊዜ አለማግኘቱና በኋላ ጢሞቴዎስ እንዲያመጣለት መጠየቁ (2ኛ ጢሞ. 4:13)፥ በድንገት መታሰሩን የሚያመለክት ይመስላል። በዚህ ጊዜ የችሎቱ ምርመራ ተስፋ የሚጣልበት ባለመሆኑ፥ ጳውሎስ 2ኛ ጢሞቴዎስን በሚጽፍበት ጊዜ የሞት ፍርድ እንደሚፈረድበት ይጠባበቅ ነበር። በዚህ ጊዜ ቤት ተከራይቶ ለመቀመጥና ከጎብኚዎች ጋር ለመነጋገር አልቻለም ነበር። ነገር ግን በሰንሰለት ታስሮ በቀዝቃዛ እስር ቤት እንዲቀመጥ ተደርጓል (2ኛ ጢሞ. 2:9)። በመሆኑም ጎብኚዎች ሊያገኙትና ሊጠይቁት አልቻሉም (2ኛ ጢሞ. 1:16–17)። ፍጻሜው እንደ ቀረበ በማወቅ፥ ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ከኤፌሶን ወደ ሮም በመምጣት የሕይወቱን የመጨረሻ ጥቂት ወራት አብሮት እንዲያሳልፍ ጠይቆታል። ስለሆነም ይህ የ2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክት የተጻፈው በሮም ከተማ ከ66–67 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ኤፌሶን ከተማ ለነበረው ጢሞቴዎስ ሳይሆን አይቀርም። 2ኛው የጢሞቴዎስ መልእክት ጳውሎስ ለእምነቱ ከመሠዋቱ በፊት የጻፈው የመጨረሻ መልእክቱ ነበር።

በዚህ የጳውሎስ የሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ይገዛ የነበረው ቄሳር ኔሮ በመባል የሚታወቅ ክፉ ሰው ነበር። ይህ ሰው ከ54–68 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የሮም ንጉሠ ነገሥት ነበር። ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ ታሪክ መጨረሻ ላይ ከኔሮ ፊት የቀረበ ሲሆን፥ በዚህ ጊዜ የተፈታ ይመስላል። በ64 ዓ.ም ግን፥ ኃይለኛ እሳት ተነሥቶ አብዛኛውን የሮም ክፍል አቃጠለ። ሕዝቡ ኔሮ እሳቱን እንዳቀጣጠለ በመግለጽ ይከሰሰው ጀመር። ምናልባትም ኔሮ ይህን ያደረገው ከብሩን የሚገልጽበትን ሕንጻ ለመገንባት የሚችልበትን ስፍራ ለማግኘት በመፈለጉ ይሆናል። ኔሮ ይህንን ክስ ለማስቀየስ ሲል በሮም ከተማ የነበሩትን ሌሎች የሕዝብ ቡድኖችን ይወቅስ ጀመር። እነዚህም የኔሮ የወቀሳ ማነጣጠሪያዎች ክርስቲያኖች ሲሆኑ፥ የተቀረው የሮም ማኅበረሰብ የእነዚህኑ ክርስቲያኖች እምነቶችና ተግባራት እንደ እንግዳ ነገር ይመለከት ነበር። በመሆኑም ሕዝቡ በክርስቲያኖችና በኔሮ ላይ ቁጣውን ይገልጽ ጀመር። በዚህም ጊዜ የኔሮ ወታደሮች በሺዎች የሚቆጠሩ

ክርስቲያኖችን በመያዝ ወደ ስፖርት ስታዲዮሞች ወሰዱቸው። በዚያም ብዙዎቹ እስከነነፍሳቸው ሲቃጠሉ የተቀሩት ከአንበሶች ጋር እንዲፋለሙ ተደርገዋል። ይህ የፀረ ክርስቲያን ስሜት እያደገ በመሄዱ፥ ስደት እየተስፋፋ ይሄድ ጀመር (1ኛና 2ኛ ጴጥሮስ)። ኔሮን ለማክበርና ለእርሱ መሥዋዕት ለማቅረብ ያልፈለጉ ክርስቲያኖች በሙሉ ለከፍተኛ ስደት ተዳረጉ። ምናልባትም ጳውሎስ የክርስቲያኖች መሪ በመሆን ይታወቅ ስለነበር ሳይሆን አይቀርም፥ እርሱና ጴጥሮስ ታስረው ወደ ሮም ተወሰዱ፥ በዚያም ኔሮ ክርስቲያኖችን ማሳደዱን ሊያቆም በተቃረበበት ወቅት ጳውሎስ አንገቱ ተቀልቶ ወደ ዘላለማዊ ቤቱ ተጉዟል።

የ2ኛ ጢሞቴዎስ ዓላማ

<u>የመጀመሪያው ዓላማ፡–</u> ጢሞቴዎስ ከሚጋፈጠው ስደት ባሻገር በእምነቱ እንዲበረታ ለማሳሰብ። በመጨረሻዎቹ ጥቂት ወራት ጳውሎስ ብቸኝነት ተጫጭኖት ነበር። ከጽሑፎቹ እንደምንመለከተው፥ ጳውሎስም እንደኛ ሰው በመሆኑ በአንዳንድ አማኞች ተግባራት ጥልቅ ስሜት ጉዳት ደርሶበት ነበር። ስደትን ከመፍራታቸው የተነሣ ይመስላል ብዙዎቹ የጳውሎስ የግል ጓደኞችና የአገልግሎት ተባባሪዎች ብቻውን ጥለውት ወደየቤቶቻቸው ገቡ። ጳውሎስ ከእስያ አውራጃ ሁሉም ሰው እንደ ተወው ይናገራል። ይህም በኤፌሶን አካባቢ የሚገኝ ስፍራ ሲሆን፥ ጳውሎስ ለረጅም ጊዜያት ያገለገለበት ቦታ ነበር (2ኛ ጢሞ. 1፡15)። አብሮት ያገለግል የነበረው ዴማስ ትቶት ሄደ (2ኛ ጢሞ. 4፡10)። እነዚህ ሰዎች በክርስቶስ ማመናቸውን ይተዉ አይተዉ የታወቀ ነገር የለም። ነገር ግን ጳውሎስ እጅግ በሚፈልጋቸው ጊዜ ትተውት መሸሻቸው በጥልቀት ጎዳው። ነገር እንደ ሉቃስ ያሉ ጥቂቶች አብረውት እስከ መጨረሻው ቆይተዋል (2ኛ ጢሞ. 4፡11)። የቅርብ ወዳጁ ጢሞቴዎስ እንኳን ከጳውሎስ ጋር ለመተባበር በመፍራቱ ምክንያት እምነቱን ለመደበቅ የሞከረ ይመስላል። ስለሆነም ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ስደትን እንዳይፈራና በእስራቱ ወይም የእስራቱና የሞቱ ምክንያት በሆነው ወንጌል እንዳያፍር ይነግረዋል (2ኛ ጢሞ. 1፡8)።

ሁለተኛ ዓላማ፡– ጳውሎስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለነበሩት ችግሮች ከሰማ በኋላ፥ ኔሮ ስደቱን እያጠናከረ ሲሄድና የሐሰት ትምህርቶች ሲስፋፉ ብዙ ሰዎች በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት እንዳይተዉ ሰግቷል። በመሆኑም ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የወንጌልን እውነት እንዲጠብቅ (2ኛ ጢሞ. 1፡14)፥ ተጨማሪ ስደት የሚያስከትልባቸው ቢሆንም (2ኛ ጢሞ. 1፡8፤ 2፡3) በአስቸጋሪ ጊዜያት ወንጌሉን መመስከራቸውን እንዲቀጥሉ (2ኛ ጢሞ. 4፡2) ለማሳሰብ ይፈልጋል። ይህ መልእክት የተጻፈው ለጢሞቴዎስ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ሁሉ ነበር። ለዚህም ነው ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡22 ላይ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን ያለው፤ ይህም የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን የሚያመለክት ነው።

ሦስተኛ ዓላማ፡– ጢሞቴዎስ በጥንቃቄ ሊይዘው በሚገባው የእግዚአብሔር ቃል ላይ አገልግሎቱን በመመሥረት በእምነቱ እንዲጸና ለማበረታታት (2ኛ ጢሞ. 2፡15)።

4ኛ ጥያቄ፡– በዘመናችን ያሉት ክርስቲያኖች እነዚህን እውነቶች በማስታወስ ተግባራዊ ማድረጋቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

የ2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክት ልዩ ባሕርያት

1. ጳውሎስ እውነትን ወይም ከሐዋርያት የተላለፈውን የእውነት አካል በመጠበቅ ላይ ያተኩራል። እዚህ ላይ ከአጽንኦት የተሰጠው አዲስን እውነት በማብራራት ወይም ሌሎች አስደሳች እውነቶችን በመፈለግ ላይ ሳይሆን፥ ጢሞቴዎስ ትክክል መሆኑን በሚያውቋት እውነት ላይ ነው። ብዙውን ጊዜ ከታላላቅ ሰባኪዎች የሚመጡትን አዳዲስና አስደሳች እውነቶች እንፈልጋለን ከታወቁ አብያተ ክርስቲያናት፥ ልዩ ስጦታ ያላቸውን ሰባኪዎች ወይም በምዕራቡ ዓለም ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የናኘ ዝና ያላቸውን አገልጋዮች ለመጋበዝ እንሽቀዳደማለን። ይህ ግን አደገኛ ነገር ነው። ምክንያቱም ጳውሎስ አስተምህሯዊ ግራ መጋባት በሚኖርበት ጊዜ ወሳኙ ነገር የእምነታችንን መሠረት መያዝና በእነዚያ እውነቶች ላይ መጽናት እንደሆነ ያስተምራል። ከጳውሎስ የተነሣው የእውነት መሥመር ለእኛና ከእኛም በኋላ ለሚመጡት ትውልዶች ይደርስ ዘንድ ተግተን ልንጠብቀው ይገባል።

2. ይህ ደብዳቤ አንድ ሽምገል ያለ ሰው ሊሞት ሲል በዕድሜው ወጣት ለሆነ ሌላ ሰው የሚያስተላልፈውን የመጨረሻ ምስክርነት ወይም ምክር ይመስላል። ጳውሎስ በዚህች አጭር ደብዳቤ ውስጥ ከሕይወት የተማራቸውን ዐበይት እውነቶች ጠቅለል አድርጎ አስቀምጧል። ከሞት ጋር ፊት ለፊት በሚጋፈጡበት ጊዜ፥ ለክርስቲያኖች ጠቀሜታ የሌላቸው እውነቶች አስፈላጊዎች አይሆኑም። የሚያስፈልጓቸው እጅግ ወሳኝ የሆኑ እውነቶች ናቸው። ለዚህም ነው ጳውሎስ ይህንን በደብዳቤው ውስጥ ያካተተው።

3. ጳውሎስ አለማፈር የሚለውን ቃል አጽንኦት ሰጥቶ ጠቅሷል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ሀ) ስለ እግዚአብሔር ለመመስከር፥ እስረኛ በሆነው በጳውሎስ (2ኛ ጢሞ. 1፡8)፥ ሐ) በወንጌል (2ኛ ጢሞ. 1፡12) እንዳያፍርና መ) ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ እንዳያፍር ታማኝ አገልጋይ ሆኖ እንዲሠራ ያስጠነቅቀዋል (2ኛ ጢሞ. 2፡15)። ጳውሎስ በኔሮ ፊት በተመረመረበት ወቅት ለእግዚአብሔር ታማኝ በመሆኑ ለኀፍረት እንደማይጋለጥ ይናገራል (2ኛ ጢሞ. 4፡16–17)።

4. ጳውሎስ አማኞችን ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማነጻጸር የታማኝ አገልጋዮችን ሚና ያብራራል። አማኞች እንደ ልጅ (2ኛ ጢሞ. 2፡1)፥ እንደ ወታደር (2ኛ ጢሞ. 2፡3–4)፥ እንደ አትሌት (2ኛ ጢሞ. 2፡5)፥ እንደ ገበሬ (2ኛ ጢሞ. 2፡6)፥ እንደ ሠራተኛ (2ኛ ጢሞ. 2፡15)፥ እንደ ዕቃ (2ኛ ጢሞ. 2፡20–21) እና እንደ ባሪያ (2ኛ ጢሞ. 2፡24) ተገልጸዋል።

5. ጳውሎስ አማኝ በክርስቶስ ኢየሱስ ላለው እምነቱ እስራትንና ሞትን እንዴት በእርጋታ እንደሚቀበል ያብራራል። ጳውሎስ ለወንጌሉ መከራን ስለ መቀበል በተደጋጋሚ ጠቅሷል። ይህም የክርስቲያኖች ተለምዷዊ አኗኗር መሆኑን በመግለጽ፥ ክርስቲያኖች መከራ በሚገጥማቸው ጊዜ ከመሸሽ ይልቅ በትዕግሥት እንዲወጡት አሳስቧል (2ኛ ጢሞ. 1፡8፥ 2፡3፥ 8–13)። ጳውሎስ ታላቅ ጀግና መሆኑን ለማሳየት አልፈለገም። ነገር ግን እግዚአብሔር

ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ላይ መሆኑንና ክርስቲያን የመንግሥተ ሰማይና የእግዚአብሔር ክብር የሚጠብቁት መሆኑን በእርጋታ ያስረዳል።

በዘመናችን፥ ስለ ስደትና ለክርስቶስ ስለ መሞት ለመነጋገር አንፈልግም። ነገር ግን በየዓመቱ 330,000 ሺህ ክርስቲያኖች ለእምነታቸው እንደሚሞቱ ጥናቶች ይጠቁማሉ። ይህ በክርስቲያኖች ላይ የሚሰነዘር ጥላቻ እየጨመረ መሄዱን የሚያሳይ ሲሆን፥ እኛም አንድ ቀን ለእምነታችን ለመሞት እንገደድ ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ከገጠመን፥ እሥራትንና ሞትን ክርስቶስን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መቀበል እንዳለብን የጳውሎስ ምሳሌነት ያስተምራል።

5ኛ ጥያቄ፡— ስደትና መከራ በሚገጥመን ጊዜ ስለ መንግሥተ ሰማይ የሚኖረን ግንዛቤና እውነት እንዴት ሊረዳን ይችላል?

የ2ኛ ጢሞቴዎስ መዋቅር

2ኛ ጢሞቴዎስ እንደ መጽሐፍ ሳይሆን ጳውሎስ ከመሞቱ በፊት የእምነት ልጁ ለሆነው ጢሞቴዎስ የሰጠውን ግላዊ ምክር የሚያስተላልፍ ሆኖ ስለቀረበ፥ ይህንንም መልእክት በአስተዋጽኦ መልክ ማቅረቡ አስቸጋሪ ነው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ በስደት ውስጥ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መመላለስ እንዳለበት አስተዋይነት የተሞላበትን ምክር ይለግሰዋል። ይህ መጽሐፍ በአራት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።

1. ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንዴት እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ለመመላለስ እንደሚችል ይመክረዋል (2ኛ ጢሞ. 1፡2)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ከፍርሃትና ዓይን አፋርነት ተላቅቆ ለእግዚአብሔር በጽናት እንዲቆምና የክርስቶስ ተከታይ በመሆኑ እንዳያፍር ያስጠነቅቀዋል። በጦርነት ውስጥ መከራ እንደሚቋቋም ብርቱ ወታደር፥ ሕይወቱን ለክርስቶስ በንጽሕና እንደሚጠብቅና ሐሰትን ለመዋጋት የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ እንደሚጠቀም አገልጋይ ሆኖ መመላለስ ያስፈልገው ነበር።

2. ጳውሎስ የሐሰት ትምህርቶች እየተስፋፉ መሄዳቸውን በመግለጽ ጢሞቴዎስ እንዴት ለእውነት ታማኝ ሆኖ ሊመላለስ እንደሚገባ ያሳስበዋል (2ኛ ጢሞ. 3)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የተጠናከረ የሐሰተኛ አስተማሪዎች ተቃውሞ እንደሚደርስበት በመግለጽ፥ ይህንኑ ለመጋፈጥ ራሱን እንዲያዘጋጅ ያሳስበዋል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተልና በተቃውሞ ፊት መንፈሳዊ ሕይወቱን እንዲጠብቅ፥ እንደዚሁም ሐሰትን ለመከላከል የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ እንዲያጠናና እንዲጠቀም ያበረታታዋል።

3. ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንዴት ታማኝ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ መኖር እንደሚችል የመጨረሻ ማደፋፈሪያ ያቀርብለታል (2ኛ ጢሞ. 4፡1—5)። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ሰዎች ለመስማት ባይፈልጉ እንኳን የእግዚአብሔርን ቃል በማሰራጨት የወንጌል መልእክተኛ ሆኖ አገልግሎቱን በታማኝነት እንዲፈጽም ያበረታታዋል።

4. ጳውሎስ እየቀረበ ስላለው ሞቱ በመግለጽ፥ ጢሞቴዎስ ወደ እርሱ እንዲመጣ ይጠይቀዋል። በተጨማሪም ለወዳጆቹ ሰላምታ ያስተላልፋል (2ኛ

ጢሞ. 4፡6-22)። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በቅርቡ እንደሚሞትና በሰማይ ግን እንደሚከብር ይነግረዋል። ጢሞቴዎስ ዮሐንስ የተባለውን ማርቆስን ይዞ እንዲመጣና ሳይሞት በፊት በቶሎ ወደ ሮም እንዲደርስ ያሳስበዋል። ጳውሎስ በችግሩ ጊዜ ትተውት የተለያዩትን ሰዎች ከዘረዘረ በኋላ፥ ድጋፍ ለሰጡት ታማኝ ሰዎች ሰላምታ ይሰጣል።

የ2ኛ ጢሞቴዎስ አስተዋጽኦ

1. ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መመላለስ እንደሚገባው ይመክረዋል (2ኛ ጢሞ. 1-2)።
   ሀ) ጳውሎስ ጢሞቴዎስ በቆራጥነት ለወንጌሉ እንዲቆም ያበረታታዋል (2ኛ ጢሞ. 1፡1-14)።
   ለ) ጳውሎስ ከሄኔሲፎሩ በስተቀር ሁሉም እንደተዉት ይናገራል (2ኛ ጢሞ. 1፡15-18)።
   ሐ) ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ታማኝ ወታደር ሆኖ ለክርስቶስ እንዲሠራ ያደፋፍረዋል (2ኛ ጢሞ. 2)።
2. ጳውሎስ የሐሰት ትምህርት እየተስፋፋ እንደሚሄድ በመግለጽ ጢሞቴዎስ ለዚህ የሐሰት ትምህርት እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥና በታማኝነት እንደሚቆም ያስገነዝበዋል (2ኛ ጢሞ. 3)።
   ሀ. ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን የሰዎች ባሕሪ ምን እንደሚመስል ያብራራል (2ኛ ጢሞ. 3፡1-9)።
   ለ. ጳውሎስ በተቃውሞና በፈተናዎች ሳይረቱ እግዚአብሔርን እንዴት በታማኝነት ማገልገል እንደሚቻል የራሱን የሕይወት ምሳሌነት ጠቅሶ ያስረዳል። ጢሞቴዎስ እርሱን በመምሰልና በመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ላይ በመደገፍ ሐሰትን እንዲከላከል ይመክረዋል (2ኛ ጢሞ. 3፡10-17)።
3. ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንዴት ታማኝ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ እንደሚኖር የማጠቃለያ ማበረታቻ ይሰጠዋል (2ኛ ጢሞ. 4፡1-5)።
4. ጳውሎስ እየቀረበ ስላለው ሞቱ በመግለጽ፥ ጢሞቴዎስ ወደ እርሱ እንዲመጣ ይጠይቀዋል፥ ለወዳጆቹም ሰላምታ ይልካል (2ኛ ጢሞ. 4፡6-22)።

ሁለተኛ ቀን — 2ኛ ጢሞቴዎስ 1-4

ከአርባ ለሚበልጡ ዓመታት ገብረ እግዚአብሔር እግዚአብሔርን በታማኝነት ሲከተል ቆይቷል። በግል ሕይወቱ፥ እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡ ለመውደድና በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደግ ሲሻ ቆይቷል። በአደባባይ ሕይወቱም እንዲሁ፥ ገብረ እግዚአብሔር በምስክርነትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ እርዳታዎችን በማድረግ እግዚአብሔርን ለማገልገል ጥሯል። ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌ ሆኖ ባይመረጥም፥ በየሳምንቱ በማለዳ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል። ይህንንም የሚያደርገው ቤተ ክርስቲያኒቱን ለአምልኮ ለማሰናዳት ነበር። የቤተ ክርስቲያን የሥራ ቀን

በሚታወጅበት ጊዜ፥ ሁልጊዜም ገብሬ ከሰዎች ቀድሞ ይመጣና ዘግይቶ ከቦታው ይሄዳል። በየቀኑ ሰፊ ጊዜ በጸሎት ያሳልፋል። በተለይም ደግሞ ለቤተ ክርስቲያኒቱና ለመጋቢው አጥብቆ ይጸልያል። የጥበቃ ሠራተኛ የሆነው ገብረ እግዚአብሔር በታማኝነቱ የታወቀ ነበር። በጊዜ ወደ ሥራው በመምጣት፥ ሳያንቀላፋ ተግቶ በመቆየትና ተግባሩን በሚገባ በማከናወን አገልግሎቱን ያበረክታል። ገብሬ ከእርጅናው የተነሣ ሥራውን ለማከናወን ባልቻለ ጊዜ በጡረታ ተገለለ። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በጠና ታሞ ሊሞት መቃረቡን ተገነዘበ። በዚህም ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ መጥቶ እንዲጠይቀው መልእክተኛ ላከበት። ወጣቱ መጋቢ ሊጸልይለት በመጣ ጊዜ፥ ገበሬ ምን ዓይነት ጸሎት ሊደረግለት እንደሚፈልግ ጠየቀው። ገብሬ ለዚህ ወጣት፥ «በጥሩ ሁኔታ ለመሞት እፈልጋለሁ። እስከ መጨረሻው ድረስ ለክርስቶስ ታማኝ መሆን አለብኝ። እርሱም መልካም አደረግህ ታማኝ ባሪያዬ እንዲለኝ እፈልጋለሁ (ማቴ. 25፡14–30)። ክርስቶስ እንደማያሳፍር መልካም ሠራተኛ እንዲያየኝ እፈልጋለሁ (2ኛ ጢሞ. 2፡15)። በክርስቶስ ካመንኩበት ዕለት ጀምሮ እርሱን በታማኝነት ለማገልገል ስሻ ኖሬአለሁ። ከፍተኛ ስጦታ አልነበረኝም፥ ትምህርት ቤት የመግባትም ዕድል አላገኘሁም። ነገር ግን እግዚአብሔር ያለኝን ሁሉ ለክብሩ እንዲጠቀምበት ፈልጌአለሁ። አሁን ሩጫዬን በመልካም ሁኔታ እንድፈጽም ጸልይልኝ።» ሲል ተናገረ።

6ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የገብረ እግዚአብሔር ባሕሪ እግዚአብሔር ከሁላችን የሚጠብቀው አመለካከት መሆኑን ግለጽ። ለ) ይህ ፍላጎት የገብሬን የዕለት ተዕለት ሕይወት እንዴት እንደ መራው አብራራ። ሐ) ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን በዓለም ከሚታወቀው ስኬት፥ ማለትም እንደ ትምህርት፥ ሀብት፥ ጥሩ ርስት፥ ወዘተ... ካሉት ነገሮች በላይ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው? መ) የራስህን ሕይወት ለመገምገም ጊዜ ውሰድ። አሁን ወደ መንግሥተ ሰማይ ብትሄድ እግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ ነበርህ የሚልህ ይመስልሃል? ካልሆነ ታማኝ አገልጋይ እንድትሆንና መንግሥተ ሰማይ በደረስህ ጊዜ መልካም አደረግህ እንድትባል ከባሕሪህና ከተግባርህ ሊለወጥ የሚገባው ምንድን ነው?

የ2ኛ ጢሞቴዎስ መጽሐፍ የተጻፈው ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሕይወቱ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ነበር። ሕይወቱን መለስ ብሎ በተመለከተ ጊዜ፥ ጳውሎስ ሕሊናው ንጹህ እንደነበረ ለመመስከር ችሏል (2ኛ ጢሞ. 1፡3)። መንፈሳዊ ሕይወቱንም በጥሩ ሁኔታ እንዳከናወነ ተረድቷል (2ኛ ጢሞ. 4፡6–8)። ያለምንም ጸጸት ከሚወደው ጌታው መልካም አደረግህ የሚሉትን ቃላት ለመስማት ወደ መንሥተ ሰማይ እየገሰገሰ ነበር። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፥ ጳውሎስ በሚሞትበት ጊዜ መልካም አደረግህ የሚሉትን እነዚሁኑ ቃላት ለመስማት የሚያስችሉትን ወሳኝ መንፈሳዊ እውነቶች ያብራራል። በዚህ አዛውንቱ ጳውሎስ ለወጣት መንፈሳዊ ልጁ በጻፈው መልእክቱ፥ እግዚአብሔርን አስከብሮ ስለመኖር የሚናገሩ ጠቃሚ እውነቶችን ዘርዝሯል።

7ኛ ጥያቄ፡– 2ኛ ጢሞ. 1–4 አንብብ። ጳውሎስ አንድ መሪ ሊያደርግና ሊሆን ስለሚገባው ነገር ጢሞቴዎስን ምን ሲል መከረው?

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት ሊመላለስ እንደሚገባ ይመክረዋል (2ኛ ጢሞ. 1–2)።

1. ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ለወንጌሉ በቆራጥነት እንዲቆም ያበረታታዋል (2ኛ ጢሞ. 1፡1–14)።

ለደት በሚነሣበት ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች በፍርሃት ይናጣሉ። በመሆኑም ብዙዎቹ መመስከር ያቆማሉ። አማኞች መሆናቸውም እንዳይታወቅ ጥረት ያደርጋሉ። አንዳንድ ፈሪ አማኞች አካባቢውን ለቅቀው ሰዎች ወደማያውቋቸው አካባቢዎች ይፈልሳሉ። ሌሎች ግን በሚታሰሩበት ጊዜ እምነታቸውን ይክዳሉ። ይህ ፍርሃት ተፈጥሯዊ ነው። እንደውም ስደትን መፍራት ወይም ሌሎች መሪዎች ምን ይሉኝ ይሆን የሚለው አስተሳሰብ ከጳውሎስ ጋር ከ15 ዓመታት ለሚበዙ ጊዜያት ያገለገለውን ጢሞቴዎስን እየተፈታተነው ነበር። ይህም የጢሞቴዎስን አገልግሎት አደናቅፎታል። ስለሆነም ሐዋርያው ጳውሎስ የ2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክቱን የጀመረው ወጣት የሥራ ጓደኛው ፍርሃቱን ተቋቁሞ እግዚአብሔርን በድፍረት እንዲያገለግል በማበረታታት ነበር። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው ምክር የሚከተሉትን ነጥቦች ይጠቅሳል፡–

ሀ) ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የነበረውን ጥልቅ ፍቅር በመግለጽ እንደሚጸልይለትና እንደገና ሊያየው እንደሚናፍቅ ይገልጽለታል።

ለ) ጳውሎስ የጢሞቴዎስን የቤተሰባዊ ውርስ፥ እንዲሁም የእናቱንና የአያቱን ጠንካራ እምነት ያስገነዝበዋል። በተጨማሪም ጢሞቴዎስ ከእግዚአብሔር ስለተቀበለው ስጦታና ጥሪ ያሳስበዋል። ምናልባትም ከሁለተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው በኋላ፥ ጳውሎስ ለወጣቱ ጢሞቴዎስ በሚጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ጢሞቴዎስ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታ የሰጠው ይመስላል። ጳውሎስ የሚናገረው ስለምን ዓይነቱ ስጦታ እንደሆነ አልተጠቀሰም። ምናልባትም በ1ኛ ጢሞ. 4፡14 ላይ የተጠቀሰው የትንቢት ስጦታ ሳይሆን አይቀርም። ምናልባትም ጢሞቴዎስ ሰዎችንና ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በመፍራቱ ምክንያት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች የማካፈሉን ስጦታ ከመጠቀም ሳይቆጠብ አልቀረም። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ፍርሃት ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ነግሮታል። ምንም እንኳን ጢሞቴዎስ ዓይናፋርና ፈሪ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ስጦታውን በሰዎች ፊት እንዲጠቀም ኃይልን ይሰጠዋል። እንዲሁም እግዚአብሔር ሰዎችን በሚያስፈርስ ሳይሆን በሚያንጽ መንገድ ስጦታውን እንዲጠቀም ፍቅርን ይሞላበታል። በተጨማሪም የራሳችንን መንፈሳዊ ሕይወት ከመገንባቱ በተጨማሪ፡ ጥራት ያለውን አገልግሎት የምንሰጥበትን ራስን የመግዛት ችሎታ ያላብሰናል። ይህም አገልግሎታችን በተከፈለ ልብ እንዳናከናውን ይረዳናል። ይህ ጥቅስ እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታውን በማሳደግ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ውጤት ማምጣት እንዳለበት ያሳያል።

8ኛ ጥያቄ፡– ሀ) መንፈሳዊ ስጦታዎችህ ምን ምንድን ናቸው? ለ) እነዚህን ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመጠቀም ምን እያደረግህ ነው? ሐ) በበለጠ

ውጤታማነት ትገለገልባቸው ዘንድ እነዚህን ስጦታዎች እያሳደግህ ያለኸው እንዴት ነው?

ሐ) ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የስደትና የሥቃይ ፍርሃቱን እንዲያሸንፍ ይነግረዋል። ሀ) በማያምኑ ሰዎች ፊት ስለ ክርስቶስ በድፍረት ለመመስከር፥ ለ) በእስር ቤት ውስጥ በሚገኘው ጳውሎስ ምክንያት ኀፍረት እንዳይሰማው ያስጠነቅቀዋል። ጢሞቴዎስ ስደትን ከመፍራቱ የተነሣ ከጳውሎስ የራቀ ይመስላል። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ መከራንና ስደትን ከእግዚአብሔር የተቀበለው ጥሪ አካል አድርጎ እንዲቀበል ያሳስበዋል። ጳውሎስ ስለ ወንጌሉ የነበረው ግንዛቤ ስደትን፥ መከራንና ሞትን ያለ ፍርሃት እንዲቀበል አስችሎታል። ወንጌል የጳውሎስን አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ሞትን የሚጋፈጥበት መንገድ ጭምር የሚለውጥ ነበር። *ክርስቶስ ሞትን እንዳሸነፈውና በወንጌሉ ለማካኝነት ሕይወትንና ዘላለማዊነትን እንዳመጣ ማመኑ ሞትን እንዳይፈራ አድርጎታል።* ጳውሎስ፥ *«ያመንሁትን አውቃለሁና የሰጠሁትንም አደራ እስክዚያ ቀን ድረስ ለመጠበቅ እንዲችል ተረድቻለሁ»* ሲል ተናግሯል። ክርስቶስ ሞትን እንዳሸነፈና የዘላለም ሕይወት ተስፋ እንደሰጠን ካመንን፥ ያ የተስፋ ቃል እውነት እንዳልሆነ በመግለጽ ሞትን እየፈራን መኖር የለብንም።

መ) ጳውሎስ ጢሞቴዎስ *የተሰጠውን መልካሙን አደራ* እንዲጠብቅ አጽንኦት ሰጥቶ ይመክረዋል። ጳውሎስ እያረጀ ሲሄድ፥ ወንጌልን በጥንቃቄ በመጠበቁ ላይ ማለትም በጤናማ ትምህርት ላይ ሊያተኩር እንመለከተዋለን። ይህንንም ያደረገው የሐሰተኛ አስተማሪዎች እንዳይበርዙት በማሰብ ነው። ጳውሎስ ወንጌሉን፥ ማለትም የክርስቶስ ኢየሱስን ሕይወትና ሞት የሚያመለክተውን እውነት እንደ ማይለወጥ እውነት ይገልጸዋል። ይህ ለባንክ ቤት ብዙ ገንዘብ በአደራ እንደ ማስረከብ ነበር። ገንዘቡ ውድ ዋጋ ስላለው በጥንቃቄ መጠበቅ አለበት። ወንጌልንም በተመለከተ እንዲህ ዓይነት እርምጃ መውሰዱ ተገቢ ነው። ወንጌሉ እንዲለወጥ ማድረጉ ወይም ሐሰተኛ እውነቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘልቀው እንዲገቡ መፍቀድ ዘራፊ ባንክ ቤት ውስጥ ገብቶ የተከማቸውን ሁሉ ከሚዘርፍበት ሁኔታ የከፋ ነው። ጢሞቴዎስ እውነትን ብቻውን ሊጠብቅ አይችልም ነበር። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እውነትን እንዲጠብቅ ሊያበረታታው ይገባ ነበር።

9ኛ ጥያቄ፡– ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የማይለወጠውን የወንጌል እውነት ማወቅና በጥንቃቄ መጠበቅ የሚያስፈልገው ለምን ይመስልሃል?

እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እውነትን እንዲያውቁና እንዲጠብቁ ይፈልጋል። ወንጌሉ በሐሰተኛ ትምህርት እንዲበረዝና እንዲለወጥ ከፈቀዱ፥ መሪዎቹ የሰዎችን ሕይወት ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታ ለአደጋ አጋልጠዋል ማለት ነው። ዋናው ነገር ክርስቲያን የሚለወጥ ስም እንደ ታፔላ ለጥፎ መዞሩ አይደለም። ደኅንነትና የዘላለም ሕይወት የሚገኙት አንድ ሰው ስለ ክርስቶስና ስለ ሞቱ ትክክለኛ እውነቶችን ሲያውቅና ክርስቶስ የሞተው በእርሱ ምትክ መሆኑን በግሉ አምኖ ሲቀበል ብቻ ነው። በዘመናችን አንድነትን ለማምጣት ስንል እውነትን እንዳንሠዋ መጠንቀቅ ይኖርብናል።

በተጨማሪም ጳውሎስ ልንከላከል እንደሚገባንና እንደማይገባን ስለሚናገራቸው ነገሮች መገንዘቡ ጠቃሚ ነው። ጳውሎስ የተወሰነ የአምልኮ ስልትን ጠብቀን ለማቆየት እንድንሞክር አላዘዘንም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ያልተቀመጠውን እውነትም እንድንጠብቅ አላስተማረም። አንዱን ቤተ እምነት በመደገፍ ሌላውን እንድንቃወምም አላዘዘንም። ይልቁንም ጤናማውን ትምህርት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተቀመጡትን መሠረታዊ የአስተምህሮ እውነቶች እንድንጠብቅ አዞናል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የቤተ እምነታችን አጽንኦት የሆነውንና የምንመርጠውን የአምልኮ ወይም የአኗኗር ስልት ከወንጌሉ አስኳል ለይተን መመልከት መቻል አለብን። ንጹህን ወንጌል ጠብቀን ለማቆየት መጣር አለብን። ነገር ግን እርስ በርሳችን ክርስቲናዊ ፍቅርና መቻቻልን በማዳበር ቤተ እምነታዊ ልዩነቶችን ከመራገብ መቆጠብ ይኖርብናል። እነዚህ ቤተ እምነታዊ ልዩነቶች የአምልኮ ስልትን ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ያልተቀመጡትን እውነቶች የሚመለከቱ ናቸው። (ልጆችን ማጥመቅ፥ ስለ መጨረሻው ዘመን ያለን አመለካከት ለዚህ ለቤተ እምነታዊ ልዩነቶች እንደ አብነት የሚጠቀሱ ናቸው።)

2. ጳውሎስ ከሄኔሲፎሩ በስተቀር ሁሉም እንደተዉት ይናገራል (2ኛ ጢሞ. 1፡15–18)።

የስደቱ ውጥረት በሮም ግዛት ሁሉ በተለይም በሮም ከተማ ያየለ ይመስላል። ኔሮ የክርስቶስ ተከታይ ነን የሚሉትን ብዙ ሰዎች ገድሎ ነበር። ሮማውያን የክርስትና መሪዎች ናቸው ብለው የሚያስቧቸው ጴጥሮስና ጳውሎስ ወኅኒ ቤት ታስረው ለእምነታቸው ሊሠዉ ተዘጋጅተው ነበር። ይህ ለክርስቲያኖች ፈታኝ ጊዜ ነበር። እንደ አለመታደል ሆኖ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ጨምሮ ብዙ ክርስቲያኖች ለእምነታቸው ለመሞት ዝግጁ አልነበሩም። በመሆኑም እምነታቸውን በመደበቅ፥ ወይም እንደ ጳውሎስ ካሉት ሰዎች ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለሰዎች ላለማሳወቅ ጥረት አድርገዋል። ጳውሎስ ከዚሁ የስደት ፍርሃት የተነሣ በእስያ ከሚገኙት አማኞች ብዙዎቹ ከእርሱ ጋር ለመተባበር እንዳልፈለጉ ገልጾአል። እስያ ኤፌሶንና በራእይ ውስጥ የተጠቀሱት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያን የሚገኙባት የሮም አውራጃ ነበረች። ጳውሎስ በዚህ መልእክት መጨረሻ ላይ ከጻፈው አሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው፥ በእምነታቸው ጸንተው የቆሙ አንዳንድ ክርስቲያኖች ነበሩ። ነገር ግን ከስደት ፍርሐት የተነሣ ብዙዎቹ እምነታቸውን ደብቀዋል።

ጳውሎስ የፊሎጎስንና የሄርዋጌኔስን ፍርሃት ከሄኔሲፎሩ ድፍረት ጋር ያነጻጽራል። እነዚህ ሰዎች በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የታወቁ መሪዎች ነበሩ። ሄኔሲፎሩ ምናልባትም የኤፌሶን ክርስቲያን ሳይሆን አይቀርም። እርሱና ቤተሰቦቹ እምነታቸውን ወይም ከጳውሎስ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለመደበቅ አልፈለጉም። እንዲያውም ጳውሎስን ለማበረታታት ሲል ሄኔሲፎሩ ወደ ሮም ተጉዟል። በዚያም ጳውሎስን እስኪያገኝ ድረስ ከተማ ለከተማ እየዞረ ፈልጎታል።

ጳውሎስ ይህን ሁኔታ በመጠቀም ሞትም የሚያስከትልብን ቢሆንም እንኳን፥ በስደት ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብን ያስረዳል። በክርስቶስ ያለንን እምነት መደበቅ የለብንም። እንዲሁም ለእምነታቸው የታሰሩትን ሰዎች ከመርዳትና ከእነርሱ ጋር ከመተባበር ወደ ኋላ ማለት የለብንም። ለወንጌሉና ለእርስ በርሳችን ሕይወታችንን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባል። ምክንያቱም ለወንጌል መሞት አማኝን ከክርስቶስ ጋር ወደሚኖርበት ዘላለማዊ ቤት የሚያደርስ በር እንደሆነ ያስተምራል። ፍርሃት ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር መፍቀድ የለብንም።

10ኛ ጥያቄ፡– በኮሚኒዝም ዘመን ለእምነቱ የታሰረ አማኝ አነጋግር። ሀ) እምነቱንና ከሌሎች ጋር የነበረውን ግንኙነት ለመደበቅ የተፈተነበት ሁኔታ እንዳለ ጠይቀው። ለ) ከዚህ ይልቅ ምን ለማድረግ መረጠ? ሐ) እግዚአብሔር በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ እንዴት እንዳበረታታው አብራራ። መ) በእስር ቤት ውስጥ ለክርስቶስ ያላቸውን ምስክርነት መጠበቃቸው፥ በእስር ቤት ውስጥ ከአማኞች ጋር ጎብረት ማድረጋቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሠ) ይህ እውነተኛ እምነት ያላቸውን ሰዎች እምነት የሚያጸናው እንዴት ነው?

3. ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ቆራጥ ወታደር ሆኖ ለክርስቶስ እንዲሠራ ያደፋፍረዋል (2ኛ ጢሞ. 2)።

ስደት ሲጠናከርና አማኞች ለእምነታቸው የመሞታቸው ጉዳይ ቁርጥ ሲሆን፥ አማኞች በተለይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊያስታውሷቸው የሚገባቸው ወሳኝ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ስለመመላለስ የሚያስተምሩ ቁልፍ እውነቶች ምን ምንድን ናቸው? እምነታችን ለቀጣዩ ትውልድ በጥንቃቄ መተላለፉን እንዴት ልናረጋግጥ እንችላለን? ጳውሎስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ታማኝ መሪ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለጢሞቴዎስ ያብራራል።

ሀ) ታማኝ የቤተ ክርስቲያን መሪ የወንጌሉን እውነት ብቃት ላላቸው ሰዎች በጥንቃቄ ያስተምራል። ይህም እምነቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይቋረጥ እንዲተላለፍ ያስችላል። ጳውሎስ የወንጌሉን ወሳኝ እውነቶች ወደጁና ሠልጣኙ ለነበረው ጢሞቴዎስ አስተላልፎአል። አሁንም ጢሞቴዎስ ታማኝ ሰዎችን ፈልጎ እነዚህን እውነቶች እንዲያስተምር ይመክረዋል። ጳውሎስ ሠልጣኞቹን የሚመርጠው በሁለት ዐበይት ብቃቶች ላይ በመመርኮዝ ነበር። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ሠልጣኞቹ ለእግዚአብሔርና ለወንጌል እውነቶች *ታማኞች* መሆን ነበረባቸው። *<u>ሁለተኛ</u>*፥ የሚመረጡት ሰዎች ሌሎችን የማስተማር ብቃት ያላቸው መሆን ነበረባቸው። ሠልጣኞቹ የተማሩትን እውነት ወስደው ለቤተ ክርስቲያን አባላት ማስተላለፍ ያስፈልጋቸው ነበር። በመጨረሻም፥ እነዚህ ጢሞቴዎስ ያሠለጠናቸው ሰዎች ሌሎችን ሰዎች ማሠልጠን ይኖርባቸዋል። በዚህ ዓይነት መንገድ የወንጌል እውነታዎች ከስሕተት ተጠብቀው ወደ እያንዳንዱ አዲስ ትውልድ ይደርሱ ነበር።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የቤተ ክርስቲያኒቱን አባላት በሙሉ ከሚያሠለጥናቸው ሰዎች ጋር እኩል በሆነ ደረጃ እንዲያስተምር አለመናገሩ ልብ ሊባል የሚገባው ነው። ጳውሎስ የሚያሠለጥናችውን ሰዎች በጥንቃቄ

እንዲመረጥ ለጢሞቴዎስ ነግሮታል። የሠለጠኑት ሰዎች ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በማስተማር የክርስቲያን እምነት ይጠብቃሉ።

11ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎችን በጥንቃቄ መምረጥና ማሠልጠን አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎችን በጥንቃቄ የሚያሠለጥኑ ይመስልሃል? ካልሆነ፥ ለምን? ሐ) የወንጌሉን መሠረታዊ እውነቶች ያስተማረ ማን ነው? መ) አንተስ እነዚህኑ መሠረታዊ እውነቶች ለማን ለማስተማር እየሞከርህ ነው? አንድን ሰው እያስተማርክ ካልሆነ፥ እየተማርክ ባለኸው እውነት እስክ አምስት የሚደርሱትን ክርስቲያን ወጣቶች እንድታስተምር እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች በልብህ ውስጥ እንዲያስቀምጥ በጸሎት ጠይቀው። ሠ) ከሌሎች ሽማግሌዎች ጋር በመመካከር፥ እነዚህን ግለሰቦች ለማስተማርና ደቀ መዝሙር ለማድረግ ፈቃድ ጠይቅ። በየሳምንቱ እነዚህን ወጣቶች የምታስተምርበት ጊዜ ወስን። 4) ለእነዚህ የአዲስ ትውልድ መሪዎች ምን እውነቶችን ማስተማር ያስፈልጋል?

ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ ስደት፥ ሞትና አጠቃላይ የአመራር ችግሮች ያሉትን በትዕግሥት መጋፈጥ ይኖርበታል። የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሰይጣንና ከመንግሥቱ ጋር እንደሚዋጋ ወታደር ነው። ስለሆነም፥ በጦር ሜዳ ላይ የሚዋጉ ወታደሮች ጉዳት እንደሚደርስባቸውና ሊሞቱም እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርበታል።

ሐ) መሪ በግል ጉዳዮች ላቢያ ከአገልግሎቱ መደናቀፍ የለበትም። ማለትም፥ *ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም*። «የጦር አዛዥ» የሆነውን ክርስቶስን በሚያስከብር መንገድ ይመላለስ ዘንድ የገንዘብን ፍቅር፥ ምቹ አኗኗር፥ የትምህርት ፍቅርና ግላዊ ክብር ወደ ጎን መተው ይኖርበታል።

መ) በውድድሩ የተደነገገውን ሕግ ተከትሎ አሎምፒክ ላይ እንደሚሮጥ አትሌት፥ የቤተ ክርስቲያን መሪ ክርስቶስ መንፈሳዊ ሩጫውን እንዲሮጥ በሰጠው ሕግጋት መሠረት ሩጫውን መቀጠል ይኖርበታል። ስለሆነም እንደ የገንዘብ ፍቅር፥ የግል ክብርና ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ማገልገል፥ ወሲባዊ ኃጢአት የመሳሰሉት ነገሮች ከሩጫው ሕግ ውጪ ናቸው። መንፈሳዊ ውድድራችንን አሸንፈን ከክርስቶስ መልካም አደረግህ የሚል የሙገሳ ቃል እንድንሰማ ከተፈለገ፥ ክርስቶስ በሰጠን ደንብ መሠረት መሮጥ ይኖርብናል።

ሠ) የቤተ ክርስቲያን መሪ የወደፊቱን ሽልማት እያስታወሰ እንዲ ትኮሕ ገበሬ ጠንክሮ መሥራት ይኖርበታል። ገበሬ መሬቱን ለማለስለስ ጠንክሮ ሲሠራ ይቆይና በመጨረሻው ዘሩን ይዘራል። ከዚያም ሲጠባበቅ ቆይቶ የመከር ጊዜ ሲደርስ አዝመራውን ይሰበስባል። በተመሳሳይ መንገድ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪ የወንጌሉን እውነቶች በመትከል ከእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ጋር በጥንቃቄ ተግባሩን ያከናውናል። ብዙውን ጊዜ ሽልማቱ የሚመጣው በምድር ላይ ሳለህ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን በሰማይ ለክርስቶስ በታማኝነት በማገልገልህ ትሸለማለህ። ስለሆነም፥ በምድር ላይ ፈጣን ሽልማቶችን ከመጠበቅ ይልቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ የመንግሥተ ሰማይን በረከቶች በጉጉት መጠበቅ ይኖርበታል።

12ኛ ጥያቄ፡— ሀ) ስለ ወታደር፥ አትሌትና ገበሬ ከተሰጠው ምሳሌ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ሌሎች ምን እውነቶችን ልትገነዘብ ትችላለህ? ለ) ሕይወትህን ገምግም። ምን ዓይነት ወታደር አትሌትና ገበሬ እንደሆንክ ራስህን መለስ ብለህ መርምር። የጦር አዛዥህ ከሆነው ከክርስቶስ ሽልማት ታገኝ ዘንድ ከሕይወትህ ሊለወጡ የሚገባቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

ረ) ሁልጊዜም የቤተ ክርስቲያን መሪ ሕይወቱና አገልግሎቱን በክርስቶስ ላይ ማተኮር አለበት። ሰዎች ስጦታዎቹን፥ ችሎታዎቹን ወይም ሥልጣኑን እንዲያደንቁለት አይፈልግም። ዋናው ነገር የክርስቶስ ወንጌል እንጂ የመሪው ሁኔታ አይደለም። ምንም እንኳን የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ ጳውሎስ ሊታሰርና ሊገደል ቢችልም፥ ማንም ሰው ሕይወት ለዋጩን የወንጌል መልእክት ሊያስር ወይም ሊገድል አይችልም። የቤተ ክርስቲያን መሪ መልእክቱ ሳይደናቀፍ ወደ ፊት ይገሰግስ ዘንድ የሚገጥመውን ችግር ሁሉ ለመቋቋም መቁረጥ ይኖርበታል።

በ2ኛ ጢሞ. 2፡11–13፥ ጳውሎስ ምናልባትም የቀድሞይቱን ቤተ ክርስቲያን መዝሙር እየጠቀሰ ይሆናል። መዝሙር በታማኝነት መመላለስ ሽልማትን እንደሚያስከትልና ክርስቶስን መካድ ደግሞ ቅጣትን እንደሚያመጣ የሚያመለክት ነው። ከክርስቶስ ጋር ከሞትን (ለኃጢአት ባሕሪያችን ስንሞትና እስከምንሞትበት ጊዜ ድረስ ለክርስቶስ በታማኝነት ስንኖር)፥ ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንኖራለን። አሁን ስደትንና መከራን ከታገስን፥ በኋላ በእርሱ ተሸልመን የንግሥናው ተካፋዮች እንሆናለን። ነገር ግን ክርስቶስን ከካድን፥ ወደ መንግሥተ ሰማይ ስንደርስ በሆነ መንገድ እርሱም እኛን ይክዳናል (ማቴ. 10፡33 አንብብ)። ጳውሎስ የሚናገረው ዓይነት ክህደት አንደኛውን ክርስቶስን ትቶ የሐሰት ጣዖታትን መከተልን የሚያመለክት ይመስላል። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ለጊዜው ታማኝነት ማጉደላችን የማይቀር ነው። ነገር ግን የሚወድደን ክርስቶስ ምን ጊዜም ታማኝነቱን ስለማያጓድልብን ልንበረታታ ይገባናል።

ሰ. የቤተ ክርስቲያን መሪ በመጨረሻ ለኃፍረት እንዳይጋለጥና ዳሩ ግን ከጌታ ዘንድ ሙገሳ እንዲሰጠው መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማጥናትና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል። ይህም በሐሰተኛ ትምህርት እንዳይወሰድ ወይም ፊሊጦስና ሄሜኔዎስ እንዳደረጉት ሰይጣን የውሸት እውነቶችን ለማሰራጨት በመሣሪያነት እንዳይጠቀምበት ይረዳዋል። ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የጠለቀ ግንኙነት የላቸውም። አንዳንዶች እንዲያውም ጊዜ ወስደው አያነቡትም። አብያተ ክርስቲያናት ወንጌሉን በማያውቁና ከዚህም የተነሣ ከሐሰት ሊጠብቋቸው በማይችሉ መሪዎች ተሞልተዋል። ያልሠለጠነና ያልተማረ የቤተ ክርስቲያን መሪ (ሽማግሌ) በቀላሉ የሰይጣን መሣሪያ ሊሆን ስለሚችል አደገኛ ነው። እንደ ፊሊጦስና ሄሜኔዎስ ሐሰተኛ ነገር አስተምረን የሰዎችን እምነት ልናናጋ እንችላለን። ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሔር እውነት የሠለጠኑ ሰዎችም መልካም ስብከት አያቀርቡም። እግዚአብሔር ሕዝቡ ሊሰማ ወደሚገባው እውነት እንዲመራቸው በጸሎት አይጠይቁትም። ሰባኪዎች እግዚአብሔር ቃሉ በተጻፈበት ጊዜ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ምን እንደሆነ

ለመረዳት ይችሉ ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ አያጠኑትም። ስለዚህም ጥቅሶችን ከዐውደ ምንባቡ ውጭ በመጠቀም ጸሐፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት ሳይረዱ ይሰብካሉ። አንዳንዶች እንዲያውም፥ መንፈስ ቅዱስ መናገር ያለብኝን ስለሚነግረኝ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የለብኝም ይላሉ። ይህ ጳውሎስ እግዚአብሔር ስለሚያመሰግነው አገልጋይ ከተናገረው ውጪ ነው። ይህ የዝግጅት ጉድለት አደገኛ በመሆኑ ሰይጣን ሐሰተኛ ትምህርቶችን ለማስፋፋት ወይም ሕዝቡ በእምነት እንዳያድግ ለመከላከል ሊጠቀምበት ይችላል።

የእውነትን ቃል በትክክል ለመያዝ ሁለት ዐበይት ነጥቦች ያስፈልጋሉ። በመጀመሪያ፥ «መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ለአማኞች በሰጠው ጊዜ የዚህ ጥቅስ ወይም ምንባብ መልእክት ምን ነበር?» የሚል ጥያቄ ማንሣት ያስፈልጋል። ይህ ጥያቄ ተፈትኖ የጠራው አገልጋይ እውነቶችን በተገለጹበት ምንባብና በጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ ዐውድ እንዲገነዘብ ይረዳዋል። ሐሰተኛ ወይም ሚዛናዊነቱን ያልጠበቀ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰርጎ ከሚገባባቸው መንገዶች አንዱ ሰዎች አንድን ጥቅስ ወይም እውነት ከዐውዱ ገንጥለው በማውጣት ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለእነሡት ርእሰ ጉዳይ ምን እንደሚል ሳያገናዝቡ መጠቀማቸው ነው። ሁለተኛው ዐቢይ ነጥብ፥ «ይህ መልእክት ለዛሬው ዘመን ምን ትምህርት ያስተላልፋል? መንፈስ ቅዱስ በዚህ ጥቅስና ምንባብ ውስጥ ያሉትን እውነቶች እንድንጠቀም የሚፈልገው እንዴት ነው?» የሚል ነው። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል የሰጠው ለዘመናትና ትውልዶች ሁሉ ነው። ነገር ግን ዛሬ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ በመቁጠር በሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ የምናደርገው እውነት መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ለአማኞች የሰጠው መሆን አለበት። ለአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሚጋፈጣቸው ሁነኛ ችግሮች ተዛማጅነት የሌሏቸውን እውነቶች ማስተማሩ አደገኛ ነው። እንዲሁም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪ የእግዚአብሔርን ቃል መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ከገለጠበት መንገድ ውጪ መጠቀሙ አደገኛ ነው።

13ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የቤተ ክርስቲያንህ አገልጋዮች የእውነትን ቃል የሚይዙበት መንገድ ጳውሎስ የተፈተኑ አገልጋዮች እንዲላቸው የሚያደርግ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ። ለ) ባለፈው ወር ውስጥ የሰማሃቸውን ስብከቶች አብራራ። ሰባኪው መንፈስ ቅዱስ ምንባቡን መጀመሪያ በገለጠ ጊዜ ሊያስተላልፍ ስለፈለገው መልእክት ትክክለኛ ግንዛቤ ያለው ይመስልሃል? ሰባኪው መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ የገለጠውን እውነት በቀጥታና በግልጽ ለዛሬው ዘመን ክርስቲያናዊ ሕይወት አዛምዱልን? ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ለገለጠው እውነት ታማኝነት እንዲኖረውና ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያንህ ሊያስተላልፍ ከሚፈልገው መልእክት ጋር ተዛማጅነት እንዲኖረው ምን ማድረግ ያሻል?

ሸ) የቤተ ክርስቲያን መሪ እግዚአብሔር ሊጠቀምበት ከፈለገ የእግዚአብሔር ንጹሕ መሣሪያ ለመሆን መወሰን አለበት። ይህም «የተቀደሰ ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ» እንዲሆን ያስችለዋል። ጳውሎስ ይህን እውነት ሁለት የሸክላ ዕቃዎችን በምሳሌነት በመጠቀም ያብራራል። ሰዎች እጃቸውን ለመታጠብ የሚጠቀሙት ዓይነት

ተራ ሳህንና ለእንግዶች ምርጥ ምግብ ለማቅረብ የሚያስችል የሸክላ ዕቃ አለ። የቤተ ክርስቲያን መሪ በሕይወቱ ውስጥ ንስሐ ያልተገባበት ኃጢአት እንዲኖር ሲፈቅድ፥ ክርስቶስ እንደ ልዩ የሸክላ ዕቃ ሊጠቀምበት አይችልም። በመሆኑም ተራ ዕቃ ይሆናል። ጳውሎስ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ክርስቶስ የሚጠቀመው ልዩ የሸክላ ዕቃ ለመሆን ሁለት ነገሮችን ማድረግ እንዳለበት ገልጾአል። በመጀመሪያ፥ *«ከክፉ የንልማሳንት ምኞት መራቅ»* አለበት። ሕይወቱንና አገልግሎቱን ከሚያቆሽሹት ኃጢአቶች (የወሲብ ኃጢአቶች፥ የገንዘብና የሥልጣን ፍቅር) መራቅ አለበት። *ሁለተኛ*፥ የኃጢአት ባሕሪውን እግዚአብሔርን በሚያስከብሩ ነገሮች መተካት አለበት። እነዚህም እንደ *ጽድቅ*፥ *እምነት*፥ *ፍቅርና ሰላም* ያሉ ናቸው።

ቀ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ከቤተ ክርስቲያን ምእመናን ጋር ያለውን ግንኙነት መጠበቅ አለበት። በተናንሽ ጉዳዮች ሐሳቡን ከማይቀበሉት ሰዎች ጋር መጣላት የለበትም። ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሲታገሉ በትዕግሥት እያስተማረ ሊረዳቸው ይገባል።

ጳውሎስ የሐሰተኛ ትምህርት እየጨመረ መሆኑን በመግለጽ ጢሞቴዎስ እንዴት ለእውነት ታማኝ ሆኖ ሊመላለስ እንደሚችል ያብራራል (2ኛ ጢሞ. 3)።

1. ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን የሰዎች ባሕሪ ምን እንደሚመስል ይገልጻል (2ኛ ጢሞ. 3፡1–9)።

ብዙውን ጊዜ ነገሮች ከዓመት ዓመት እየተሻሻሉ ይሄዳሉ ብለን እናስባለን። ብዙ ሰዎች ትምህርት የተከታተሉ አዳዲስ ሥራዎችን በመፍጠር ብዙ ገንዘብ ያገኛሉ፥ ከግብርና ቦታቸው ራቅ ባሉ አካባቢዎች የተሻሉ ቤቶችን ይሠራሉ፥ የራሳቸውን ቴሌቪዥን፥ መኪና ወዘተ... ይገዛሉ። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን በመሳሰሉ ተቋማት አማካኝነት በዓለም ላይ ብዙ ገንዘብና ብዙ ሥራም ማግኘት ይቻላል። ይሁንና ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ዓለምን ሲመለከት ሰዎች ወደ መጨረሻው ዓለም እየቀረቡ በሚመጡበት ጊዜ ዓለም የበለጠ በክፋት እንደምትሞላ ተገንዝቧል። ትምህርትና ሥልጣኔ በመጨረሻው ዘመን ላይ አዎንታዊ ገጽታ ከማሳየት ይልቅ አሉታዊ ጥላ ያጠላል። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ በመጨረሻው ዘመን የሚለወጡትን አንዳንድ ነገሮች ጠቃቅሷል።

ሀ) ሰዎች ከመጠን በላይ ራስ ወዳድ በመሆን ደስ ያሰኛቸውን እያደረጉ ለራሳቸው ብቻ ይኖራሉ። እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ነገር ግድ አይኖራቸውም። ሃይማኖተኞችና መንፈሳውያን ቢመስሉም፥ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት አይኖራቸውም። *(የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል።)*

ለ) ሰዎች ሌሎችን ለራሳቸው ፍላጎት በማገልገል እውነት እንዳይስፋፋ ያደርጋሉ። ጳውሎስ ሙሴን የተቃወሙትን ሁለት ሰዎች ማለትም አያኔስንና ኢያንበሬስን ይጠቅሳል። እነዚህ ሁለት ሰዎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ አልተጠቀሱም። ነገር ግን በአይሁድ ትውፊቶች ውስጥ ሙሴን የተቃወሙ የግብጻውያን የችሎት አስማተኞች መሆናቸው ተገልጾአል (ዘጸ. 7፡11)።

14ኛ ጥያቄ፡– በወላጆችህ ዘመን የነበረውን የሥነ ምግባር መመዘኛ ዛሬ ከብዙ ወጣቶች (ክርስቲያኖችን ጨምሮ) ከምንመለከተው የሥነ ምግባር መመዘኛ ጋር አነጻጽር። ተቀባይነት ያላቸው ልምምዶች ጳውሎስ ከገለጻቸው ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? ይህ ክርስቶስ ወደሚመለስበት የመጨረሻው ዘመን እየቀረብን መሄዳችንን የሚያመለክተው እንዴት ነው?

2. ጳውሎስ ከተቃውሞና ፈተናዎች ባሻገር እግዚአብሔርን እንዴት በታማኝነት ማገልገል እንደሚያሻ የራሱን ምሳሌነት ጠቅሶ ያብራራል። ጢሞቴዎስ ሐሰትን ለመዋጋት የጳውሎስን ሕይወት መከተልና ቅዱሳት መጻሕፍትን መጠቀም ያስፈልገው ነበር (2ኛ ጢሞ. 3፡10–17)።

ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን ሲያስብ፥ ሁለት የሕይወት መንገዶችን ያነጻጽራል። አጠቃላዩ ማኅበረሰብ አንዱ ሌላውን ለማታለል ሲሞክር ሰይጣን ደግሞ የበለጠ ያታልላቸዋል። እነዚህ ሰዎች ከፈሪሃ እግዚአብሔር ርቀው የተሳካ ሕይወት ለመኖር የቻሉ ቢመስላቸውም፥ የኋላ ኋላ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።

ከዚህ በተቃራኒ ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተል ያበረታታዋል። ምንም እንኳን ጳውሎስ ለጊዜው ስደት ቢደርስበትም፥ ሕይወቱን የኖረው ዓላማ ባለው መልኩ ነበር። ይኸውም ወንጌልን በዓለም ሁሉ ማድረስ ነበር። በስደት ጊዜ ታጋሽ፥ ለሰዎች ፍቅርን የሚገልጽና ክርስቶስ በሁኔታዎች ሁሉ እንደሚረዳው የሚተማመን አገልጋይ ሆኖ ተመላልሷል። እያደር እየተናደ በሚሄድ የሕይወት ጠርዝ ላይ ሆኖ ጢሞቴዎስ በእግዚአብሔር ቃል ላይ አጽንኦት እንዲሰጥ ጳውሎስ ያደፋፍረዋል። የእግዚአብሔርን ፍጹማዊ እውነት የሚያገኘው ከቃሉ ነውና። ጳውሎስ የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች የፈጠሩት አለመሆኑን ይገልጻል። ነገር ግን እግዚአብሔር አጽናፈ ዓለሙን በቃሉ ትእዛዝ እንደፈጠረ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ሁሉ የመነጨው ከእርሱ ነው። ጢሞቴዎስ ሐሰተኛ ትምህርትን ለመከላከል መጽሐፍ ቅዱስን በዋናነት መጠቀም ያስፈልገው ነበር። ጢሞቴዎስ እውነትን *ለማስተማር*፥ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ የማይመላለሱትን ሰዎች *ለመገሠጽ*፥ ግራ የተጋቡትን *ለማረምና* ሰዎችን በጽድቅ ጎዳና *ለማሠልጠን* የእግዚአብሔርን ቃል መጠቀም ነበረበት።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋይ ሆኖ ሊኖር ስለሚችልበት መንገድ የማጠቃለያ ማበረታቻ ይሰጠዋል (2ኛ ጢሞ. 4፡1–5)።

ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪ ተግባር ምን መሆን እንዳለበት ጠቅለል አድርጎ በመግለጽ ለጢሞቴዎስ ያቀረበውን ምክር ይደመድማል። ጢሞቴዎስ እግዚአብሔር ሕይወቱን እየተመለከተ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልገው ነበር። አንድ ቀን ደግሞ *በሕያዋንና በሙታን ላይ በሚፈርድ* በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ይቀርባል። አንድ መሪ ምን ማድረግ እንዳለበት፥ እንዴት መምራት እንዳለበት ወይም የስኬታማ አመራር ምሥጢሮች ምን ምን እንደሆኑ የሚያብራሩ ብዙ ሊቆች አሉ። ምንም እንኳ የእነዚህ ሊቃውንት ምክር

ጠቃሚ ቢሆንም፥ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እጅግ ጠቃሚ እውነቶችን ዘርዝሯል።

ሀ) መሪ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ጊዜው አመቺ ሆኖ ሰዎች ስብከቱን በሚሰሙበት ጊዜ (በጊዜውም) ወይም ጊዜው አስቸጋሪ ሲሆንና ሰዎች ስብከቱን በማይቀበሉበት ጊዜ (አለጊዜውም)፥ ሕዝቡን የማረም፥ የመገሠጽና የማበረታታት ተግባሩን ማከናወን አለበት። ዘለቄታዊ ውጤት የሚያመጣው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። ከዘመኑ የአመራር ሊቃውንት የሚመጡ ምክሮች ወይም ፈውሶችና ተአምራት የእግዚአብሔርን ቃል ያህል ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ አይችሉም። የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር አስፈላጊ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት እየቀረበ በሚመጣበት ጊዜ፥ ብዙ ሰዎች እውነትን ለመስማት የማይፈልጉ መሆናቸው ነው። ሰዎች የሚሰሙት የሚፈልጉትን ስብከት ብቻ ይሆናል። እነዚህም ሰባኪዎች ሕዝቡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ሳይሆን ጊዜያዊ ስሜታቸውን በሚኮረኩሩ ነገሮች ላይ ያተኩራሉ።

ለ) መሪ በተለዋዋጭ ጊዜያትና ሁኔታዎች ግር መሰኘት ወይም መፍራት የለበትም። ሁሉንም ተቋቁሞ በርጋታ መመላለስ ይኖርበታል።

ሐ) መሪ እግዚአብሔር እንዲያልፍ በሚጠይቀው መከራ ሁሉ ውስጥ ማለፍ አለበት። የመሪነት ጎዳና ቀላል አይደለም። ከቤተ ክርስቲያንም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ችግሮች ይገጥሙታል። ነገር ግን በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ከልጆቹ ጋር ነው።

መ) መሪ ዓይኖቹን ከእግዚአብሔር በተቀበላቸው ኃላፊነት ላይ ማኖር አለበት። መሪ በቀላሉ ዓላማውን ሊስትና እግዚአብሔር ያልጠራውን አገልግሎት ለማከናወን ሊሯሯጥ ይችላል። ነገር ግን መሪ እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታ ተጠቅሞ ዓላማውን ማከናወኑ ወሳኝ ነው። ጢሞቴዎስ ለጠፉት ወንጌልን እየሰበከና የወንጌላዊነት ተግባሩን እየተወጣ ቤተ ክርስቲያንን የመገንባት ተግባሩን ማከናወን ነበረበት። ጢሞቴዎስ በአንድ ቦታ መቀመጥ የሚገባው መጋቢ ሳይሆን፥ ለጠፉት የመመስከርና የተዳከሙትን አብያተ ክርስቲያናት የማጠንከር ጸጋ የተሰጠው አገልጋይ ነበር።

15ኛ ጥያቄ፡– ሀ) እግዚአብሔር ምን ዓይነት ስጦታዎች ወይም ጥሪ የሰጠህ ይመስልሃል? ለ) ይህንኑ ተግባር እንዴት እያከናወንህ ነው? ሐ) እግዚአብሔር የሰጠህን ስጦታና ጥሪ ትቶ ወደ ሌላ አገልግሎት መግባት የሚያስከትላቸው ፈተናዎች ምን ምንድን ናቸው? መ) ጳውሎስ ከላይ ያቀረባቸው ትእዛዛት እግዚአብሔር ከአያንዳንዱ መሪ ሕይወት የሚፈልገውን አገልግሎት የሚገልጹት እንዴት ነው?

ጳውሎስ እየቀረበ ስላለው ሞቱ በመግለጽ ጢሞቴዎስ ወደ እርሱ እንዲመጣ ይጠይቃል። ለወዳጆቹም ሰላምታ ይልካል (2ኛ ጢሞ. 4፡6–22)።

ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ ያጠቃለለው የቅርብ ጓደኛውና መንፈሳዊ ልጁ ለነበረው ጢሞቴዎስ የሚሞትበት ጊዜ እንደቀረበ በመግለጽ ነው። ቀደም ሲል ከፍርድ ችሎቱ ሲቀርብ ወዳጆቹ ሁሉ ትተውት ራቁ። ፍርዱም በጳውሎስ ላይ እየጠነከረ መጣ። ነገር ግን ጳውሎስ መራር ከመሆን ይልቅ፥ እግዚአብሔር በቅርብ እንደረዳውና ወንጌሉን ለማሰራጨት እንዳስቻለው ገልጾል። ጳውሎስ ለጊዜው ከአንበሳ አፍ ድኖ ነበር። ይህ ተምሳሌታዊ አገላለጽ የሚያመለክተው ጳውሎስ በቅርቡ እንደሚገደል ነው። ምክንያቱም የሮም ዜግነት ያላቸው ሰዎች በአንበሶች ተበልተው እንዲሞቱ አይደረግም ነበር።

አሁን ግን ጳውሎስ የሞትን ፍርድ ወደሚቀበልበት ችሎት እየቀረበ ነበር። በመሆኑም ጳውሎስ የራሱን ሕይወት ይገመግማል። ጳውሎስ ራሱን የተመለከተው እንደ ሰማዕት ወይም አሳዛኝ ሁኔታ እንደሚደርስበት ሰው አልነበረም። ይልቁንም ራሱን እንደ መጠጥ መሥዋዕት ይቆጥረዋል። በብሉይ ኪዳን ዘመን ከእንስሳት መሥዋዕት ጋር ከመሠዊያው ሥር የሚፈስ የወይን መሥዋዕት ይቀርብ ነበር። ይህም አይሁዶች እግዚአብሔር ለሰጣቸው በረከት ምሥጋና የሚያቀርቡበት መንገድ ነበር (ዘኍል. 15፡1–12፥ 28፡7፥ 24)። ጳውሎስ ሕይወቱ ለሚወደው ክርስቶስ የቀረበ መሥዋዕት መሆኑን ተመለከተ። ክርስቶስ ደግሞ ለሰዎች ሕይወቱን የሰጠ ዋንኛው መሥዋዕት ነበር። ጳውሎስ በሕይወት ቢኖር ኖሮ ሕይወቱ ሕያው መሥዋዕት ይሆን ነበር (ሮሜ 12፡1–2)። ቢሞት ደግሞ ሕይወቱን ለክርስቶስ በፍቅርና በምስጋና መልሶ ያስረክበዋል። እናም የመሥዋዕትነት ሞት ይሞታል። ጳውሎስ ሕይወቱንና መንፈሳዊ ሩጫውን መለስ ብሎ ሲመለከት፥ ለክርስቶስ ታማኝ ሆኖ መልካሙን ሩጫ ስለሮጠ እግዚአብሔርን ያመሰግናል። ጳውሎስ ወደፊት አሻግሮ በሚመለከትበት ጊዜ ክርስቶስ የጽድቅን አክሊል እንደሚሸልመው ያውቅ ነበር። በጥንት ዘመን አትሌቶች በስፖርት አሸናፊ በሚሆኑበት ጊዜ ከወይንና ከአበባ የተሠራ አክሊል በራሳቸው ላይ ይደረግላቸው ነበር። ነገር ግን መንፈሳዊ ሩጫ ለሚሮጡ ሰዎች ጳውሎስ የተሻለ ሽልማት እንደሚሰጣቸው ይናገራል። ይህም የጽድቅ አክሊል ነው። ጳውሎስ በችሎት ፊት ቀርቦ ሞት እንደሚፈርድበት ቢያውቅም፥ ሞቱ ሽንፈት ሳይሆን እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊወስደው የተጠቀመበት መንገድ መሆኑን ተረድቷል።

ጳውሎስ ከመሞቱ በፊት ጢሞቴዎስና ዮሐንስ ማርቆስ ወደ ሮም መጥተው ከእርሱና ከሉቃስ ጋር እንዲገናኙ ይፈልጋል። ጢሞቴዎስ በርኖሱን ይዘለት እንዲመጣ ጠይቋል። ይህም ከእስር ቤቱ ብርድ ይከላከለው ነበር። በተጨማሪም የብራና መጽሐፉን (ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱሱን እንዲያመጣለትም ጠይቆታል።)

ጳውሎስ ስለ አንዳንድ የሥራ ጓደኞቹም ጽፏአል። ከጳውሎስና ጢሞቴዎስ ጋር ሲሠራ የቆየው (ቆላ. 4፡14) ዴማስ ከፍርሃት ወይም ከከፉ አሳብ የተነሣ ጳውሎስን ትቶ ወደ ቤቱ ተመልሷል። ቲቶና ቄርቂስን እንዲሁ ወደ ሌላ ስፍራ ሄደዋል። እነርሱ የሄዱት ምናልባት ለአገልግሎት ይሆናል። ኤርስጦስ ጳውሎስ ወዳለበት ወደ ሮም ሊመጣ አልቻለም። ነገር

ግን በቆሮንቶስ ማገልገሉን ቀጠለ። ሌላው የእነጳውሎስ የአገልግሎት ጓደኛ ጥሮፊሞስን ታሞ በሚሊጢን ቀረ።

ጳውሎስ በጢሞቴዎስ በኩል ለአንዳንድ ልዩ ጓደኞቹ ሰላምታ በመላክ ይህንን መልእክት ይፈጽማል። እነዚህም አቂላ፥ ጵርስቅላና የሄኔሲፎሩ ቤተሰቦች ናቸው። እንዲሁም ጳውሎስ ከእርሱ ጋር የነበሩት ጥቂት ክርስቲያኖች ለጢሞቴዎስ ያስተላለፉትን ሰላምታ አቅርቧል።

16ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የመጨረሻዎቹ የጳውሎስ ቀናት የምንሞትበት ጊዜ በሚቃረብበት ወቅት ሊኖረን ስለሚገባው አመለካከት መልካም ምሳሌዎች የሚሆኑት እንዴት ነው። ለ) የጳውሎስ የመጨረሻው መልእክት ከሆነው የ2ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ ለመንፈሳዊ ሩጫ መሠረታዊ የሆኑትን ትምህርቶች ዘርዝር። ሐ) ከዚህ መልእክት የተፈተነ አገልጋይ ስለመሆን ምን እንማራለን?

ሦስተኛ ቀን — የቲቶ መግቢያ

«አንተ ግን ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን ተናገር። ሽማግሌዎች ልከኞች፥ ጭምቶች፥ ራሳቸውን የሚገዙ፥ በእምነትና በፍቅር በመጽናትም ጤናሞች እንዲሆኑ ምከራቸው። እንዲሁም አሮጊቶች ሴቶች አካሄዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የሚገባ... አስተምራቸው። ጎበዞችም እንዲሁ ራሳቸውን እንዲገዙ ምከራቸው... ባሪያዎች... ምከራቸው» (ቲቶ 2፡1–9)።

አንድ ጊዜ አንድ ታዋቂ አፍሪካዊ ክርስቲያን በአፍሪካ ውስጥ ክርስትና ሁለት ኪሎ ሜትር ስፋትና ሁለት ሴንቲ ሜትር ጥልቀት አለው ሲል ተናግሮ ነበር። ይህን ሲል በአፍሪካ ውስጥ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ብዙ ሰዎች እንዳሉ መግለጹ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔርንና ቃሉን በማወቅ አላደጉም። ይህን ክርስቲያን ወንድም ያሳሰበው በአፍሪካ የሚገኙ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ እውነትን አለመማራቸውና ተገቢውን ክርስቲያናዊ ሕይወት የማይኖሩና ለሐሰት ትምህርቶች የተጋለጡ መሆናቸው ነበር።

ቲቶ ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲያደራጁ ከወከላቸው አገልጋዮች አንዱ ነበር። ጳውሎስ ለቲቶ በጻፈው መልእክቱ በማስተማር ተግባር እንዲተጋ በተደጋጋሚ አሳስቦታል። ልጆች፥ ወጣት ወንዶች፥ ወጣት ሴቶች፥ አረጋውያን ሴቶችንና አረጋውያን ወንዶችን ጨምሮ ሁሉም የዕድሜ ክልሎች፥ እንዲሁም ባሮችን ጨምሮ በሁሉም የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መማር እንዳለባቸው ጳውሎስ ለቲቶ አሳስቧል። እነዚህ ሰዎች በሁለት መንገዶች መማር ነበረባቸው። <u>በመጀመሪያ</u>፥ አማኞች የእግዚአብሔርን እውነቶች መማር ያስፈልጋቸው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ መንፈስ ቅዱስ፥ ደኅንነት፥ ወዘተ... የሚያስተምረውን ማወቅ ያስፈልጋቸዋል። ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ቃል እነዚህን እውነቶች ሳያውቅ በእምነቱ ሥር ሊሰድ አይችልም። ትላልቅ ዛፎች በጥልቅ እንደሚሰዱት ሥር እነዚህ እውነቶች የሰው ሕይወት እንዲጸናና የሐሰተኛ አስተምህሮ ወይም የስደትን ነፋሳት እንዲቋቋም ያስችሉታል።

<u>ሁለተኛ</u>፥ አማኞች ባሕሪያቸውን እንዲቀይሩ መማር አለባቸው። የቀርጤስ ሰዎች በሮም ግዛት ውስጥ በውሸተኝነታቸው፥ በክፋታቸው፥ እንዲሁም ሰነፎችና ሆዳሞች በመሆናቸው ይታወቁ ነበር (ቲቶ 1፡12)።

እንዲህ ዓይነቱ ባህሪ በክርስቶስ ላይ ካለህ እምነትና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አዲስ ፍጥረት ከመሆን ጋር የሚጣጣም አልነበረም። ይልቁንም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ባላቸው ግንኙነት መንፈስ ቅዱስ የማይበሳጩ፥ ክብር የሚገባቸው፥ ራሳቸውን የሚገዙ፥ ጤናማ እምነት ያላቸው፥ አፍቃሪዎችና ታጋሾች፥ የማይሰርቁ፥ ወዘተ... አድርጎ እንዲለውጣቸው መጣር ያስፈልጋቸው ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል የምንማርበትና የምናስተምርበት ዋናው ዓላማ አዳዲስ እውነቶችን ማወቅ ብቻ አይደለም። (ለምሳሌ፥ የዳዊት አባት ማን እንደሆነ ማወቅ)። ነገር ግን ባህሪያችን እንዲለወጥና እኛኗራችንም የተስተካከለ እንዲሆን የእግዚአብሔርን ቃል እንማራለን። ጳውሎስ እንደ መጠጣት፥ ፊልም ማየት፥ አለባበስ በመሳሰሉት አንዳንድ ሕጎች ወይም ደንቦች ላይ አጽንኦት አለመስጠቱ ልብ ሊባል የሚገባው ነው። ነገር ግን የጳውሎስ ትምህርት በሰዎች ባሕሪ ላይ ያተኩራል፥ ምክንያቱም አተገባበራችንን የሚወስነው ባሕሪያችን ነውና።

ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ዋናው ማስተማር እንደሆነ ለቲቶ ያስረዳል። ጤናማ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ደኅንነትን ላላገኙ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ላመኑት ክርስቲያኖችም እምነታቸውን የሚያጸና ትምህርት በማቅረብ ትተጋለች። በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያድጉ ዘንድ በሁሉም የዕድሜ ክልል ለሚገኙ ሰዎች ተዛማጅነት ያላቸው የሥልጠና ፕሮግራሞች ይሰጣሉ።

17ኛ ጥያቄ፦ ሀ) የቤተ ክርስቲያንህን የትምህርት ፕሮግራሞች መርምር። በሁሉም የዕድሜ ክልሎች የሚገኙ አማኞች ትምህርት እያገኙባቸው ያሉባቸውን መንገዶች ግለጽ። ለ) ትምህርቱ የሚያተኩረው የተወሰኑ መረጃዎችን፥ ደንቦችና ሕጎችን በማወቅ ላይ ነው? ወይስ የአኗኗር ለውጥን በሚያስከትለው ባሕሪ ላይ? ሐ) ቤተ ክርስቲያንህ ያልዳኑትን ሰዎች ወደ ክርስቶስ ለማምጣትና አማኞች በሕይወታቸው እንዲያድጉ ለማገዝ የምታቀርባቸውን ትምህርቶችና ስብከቶች ሚዛናዊ ታደርጋለች? መልስህን አብራራ። መ) ቤተ ክርስቲያንህ እንዴት የተጠናከረ የትምህርት ፕሮግራም ልትዘረጋ እንደምትችል የበኩልህን አስተያየት ስጥ።

የቲቶ መልእክት ከመጋቢያዊ መልእክቶች አንዱ ሲሆን፥ ጳውሎስ ቲቶ የቤተ ክርስቲያንን አመራር ስለሚያደራጅበት መንገድ የሰጠውን ማብራሪያ ያካትታል። ምንም እንኳ የቲቶ መልእክት የተጻፈው የ1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክቶች በተጻፉበት ጊዜ ቢሆንም፥ ቀደምት የእምነት አባቶች 2ኛ ጢሞቴዎስን ተከትሎ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲሰፍር አድርገውታል። ይህንንም ያደረጉት የ1ኛና የ2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክቶች ጎን ለጎን እንዲቀመጡ በማሰብ ነው።

18ኛ ጥያቄ፦ ስለ ቲቶ ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አንብብ። ስለ ደራሲው፥ መልእክቱን ስለሚቀበሉት ሰዎችና ስለ መጽሐፉ የተሰጠውን ማብራሪያ ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

የቲቶ መልእክት ደራሲ

19ኛ ጥያቄ፦ ቲቶ 1፡1–3 አንብብ። ሀ) የቲቶ መልእክት ደራሲ ማን ነው? ለ) ደራሲው ራሱን የገለጸው እንዴት ነው? ይህ በ1ኛ ጢሞ. 1፡1 ራሱን ከገለጸበት

ሁኔታ ጋር የሚመሳሰለውና የሚለያየው እንዴት ነው? ይህ ደራሲው በዚህ መልእክት ውስጥ ስላተኮረበት አሳብ ምን ያሳያል?

ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ ባልተለመደ ሁኔታ ለቲቶ ረጅም መግቢያ ሰጥቷል። በተለመደው ስያሜው ራሱን «የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ» ብሎ ከመጥራቱ በተጨማሪ፥ ሁለተኛውንና በጣም የሚወደውን ስም «የእግዚአብሔር ባሪያ» የሚለውንም ይጠቀማል። ጳውሎስ በሐዋርያነቱና በሥልጣኑ ላይ በማተኮር ሊኩራራ ቢችልም፥ የሐዋርያነት ሥልጣኑን ከባሪያነት አመለካከት ጋር ሚዛናዊ አድርጎ ገልጾአል። ጳውሎስ ክርስቶስ የሚጠይቀውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ፈቃደኛ ነበር። ይህም በቀዳሚነት ለሌሎች ክርስቲያኖች በሚያበረክተው አገልግሎት ተመልክቷል። ስለሆነም ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ሁሉ መሪዎች ሊከተሉት የሚገባው መልካም ምሳሌ ነው። የሽማግሌነት ሥልጣን ቢኖረንም፥ አመለካከታችን ሌሎችን በማገልገልና እግዚአብሔርን በማገልገል ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል።

ጳውሎስ በዚህ በቲቶ በጻፈው መልእክቱ መግቢያ ላይ በሁለት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል። በመጀመሪያ፥ የአማኞች እምነት ስለተመሠረተበት እውነት ይናገራል። ጳውሎስ ይህ እውነት ከማይዋሽ አምላክ የመነጨ መሆኑን ያስረዳል። ይህም እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ለሕዝቡ በሰጣቸው የተስፋ ቃሎች ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም የተስፋ ቃል ደኅንነትን ብቻ ሳይሆን ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር መኖርንም የሚያጠቃልል ነው። ሁለተኛ፥ ይህን እውነት ከማመን የሚመጣ መንፈሳዊነት አለ። እግዚአብሔር ሊያድነን የሚፈልገው ከሲኦል እንድናመልጥ ብቻ አይደለም። በባሕሪያችንና በተግባራችንም መንፈሳውያን እንድንሆን ይፈልጋል።

20ኛ ጥያቄ፡— ሀ) እውነትና መንፈሳዊነት የሚሉት እነዚህ ሁለት ቃላት የአዲስ ኪዳን መልእክት ማጠቃለያ የሆነው የእምነት ውጤቶች መሆናቸውን ግለጽ። ለ) ቤተ ክርስቲያንህ ከእነዚህ ሁለት ነገሮች በየትኛው ላይ የበለጠ ታተኩራለች? ሐ) እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት እንድንኖር እነዚህ ሁለት ነገሮች አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈው ለማን ነው?

ጳውሎስ ይህን መልእክት ለማን እንደላከ ሲገልጽ፥ «በጋይማኖት ጎብረት እውነተኛ ልጄ ለሚሆን ለቲቶ» ይላል። ቲቶ በሁለት ልዩ መንገዶች የጳውሎስ ልጅ ነበር። በመጀመሪያ፥ ቲቶ የጳውሎስ መንፈሳዊ ልጅ ነበር። ምናልባትም ቲቶ በክርስቶስ እንዲያምን በመጣሪያነት ያገለገለው ጳውሎስ ሳይሆን አይቀርም። ሁለተኛ፥ ቲቶ ከጳውሎስ፥ የቅርብ ጓደኞችና የጉዞ ባልደረቦች አንዱ በመሆኑ የጳውሎስ ልጅ ነበር።

21ኛ ጥያቄ፡— እነዚህን ጥቅሶች በማንበብ በጳውሎስና ቲቶ መካከል የነበረውን ግንኙነት አብራራ። ገላ. 2፡1–3፥ 2ኛ ቆሮ. 2፡13፥ 7፡5–14፥ 8፡16–23፥ 2ኛ ጢሞ. 4፡10።

ስለ ቲቶ ብዙ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም። ማንነቱ፥ የመጣበት አካባቢ፥ ወዘተ... በዝርዝር ሰፍሮ አንመለከትም። ምንም እንኳ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሶ ባይገኝም፥ የጳውሎስ መልእክቶች

እንደሚያሳዩት ቲቶ ከጳውሎስ የቅርብ ባልደረቦችና የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞዎቹ አጋሮች አንዱ ሳይሆን አይቀርም። በመጀመሪያ ስለ ቲቶ የምናነበው ከገላትያ መልእክት ውስጥ ነው። በገላትያ መልእክት ውስጥ ቲቶ አሕዛብ ሲሆን፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት መገረዝ የሚያስፈልገው መልካም የአሕዛብ አማኝ ምሳሌ ሆኖ ተጠቅሷል። ይህ ከፊል አሕዛብና ከፊል አይሁዳዊ ሆኖ ሳለ ጳውሎስ ከገረዘው የጢሞቴዎስ ሁኔታ የተለየ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ቲቶ ከገላትያ ወይም ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መምጣቱን አይናገርም። በተጨማሪም ከመጀመሪያው የጳውሎስና የበርናባስ የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞ በኋላ ማመን አለማመኑ አልተጠቀሰም።

የአሕዛብ ክርስቲያኖች መገረዝ አለባቸው ወይም የለባቸውም የሚለው ክርክር በተጧጧፈበት ወቅት ጳውሎስና በርናባስ ቲቶን ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት። ቲቶ የተመረጠው ምናልባትም ጥልቅ መንፈሳዊነት የነበረው ሰው በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስና በርናባስ አሕዛብ ክርስቲያን መገረዝ ሳያስፈልገው በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላና የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ ሊመላለስ እንደሚችል ለአይሁድ ክርስቲያኖች ለማሳየት ፈልገው ነበር። የቲቶን መንፈሳዊነት መመልከታቸው የአይሁድ መሪዎች የአሕዛብ ክርስቲያኖች ደኅንነትን ለማግኘት መገረዝ አለባቸው በሚለው ክርክር ላይ ሚዛናዊ አመለካከት እንዲይዙ ሳይረዳቸው አልቀረም። የአይሁድ መሪዎች ቲቶ ባይገረዝም እንደ ክርስቲያን ሊቀበሉት ችለዋል።

ቲቶ ከጳውሎስ የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞዎች ውስጥ በምን ያህሎቹ ላይ አብሮ እንደተጓዘ አልተጠቀሰም። ነገር ግን ከጳውሎስ ጋር ለረጅም ጊዜ በማገልገሉ ምክንያት ለትላልቅ አገልግሎቶች እንደ ተሾመ እንመለከታለን። በጳውሎስ ሦስተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው ላይ፥ ቲቶ ከጳውሎስ ጋር በኤፌሶን ነበር። ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስን ከጻፈ በኋላ በእርሱና በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። ቲቶ መልካም የአስተዳዳሪነት ስጦታ የነበረውና እንደ ጢሞቴዎስ መጋፈጥን የሚፈራ ሰው አልነበረም። በመሆኑም ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የነበሩትን ችግሮች በማስተካከል ለኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ገንዘብ የማሰባሰቡን ተግባር እንዲጀምሩ ያበረታታቸው ዘንድ ቲቶን ወደ ቆሮንቶስ ላከው። ምናልባትም የጠፋውንና 2ኛው የቆሮንቶስ መልእክት በመባል የሚታወቀውን ለክርስቲያኖች የወሰደው ቲቶ ሳይሆን አይቀርም። ቲቶ በቆሮንቶስ የነበረውን ሁኔታ በዘዴ ለማስተካከል ችሏል። ቲቶ በመቄዶንያ ከጳውሎስ ጋር በተገናኘ ጊዜ፥ ክርስቲያኖች ለጳውሎስ የነበራቸውን አመለካከት ቀይረው ነበር። በዚህ ጊዜ ጳውሎስ 2ኛ ቆሮንቶስን ጽፎ በቲቶ በኩል ወደ ቆሮንቶስ ላከ። ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ፍቅር የነበረው ቲቶ ክርስቲያኖች የጳውሎስን መመሪያዎች በመከተል ለኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ገንዘብ የማሰባሰቡን ተግባር እንዲጀምሩ ሊረዳቸው ችሏል። ጳውሎስ ቲቶን እንደ ባልደረባውና የወንጌል አገልግሎት ተባባሪ አድርጎ ይቆጥረውና ያከብረው ነበር።

ጳውሎስ ታስሮ በቆየባቸው ሁለት ዓመታት ውስጥ ቲቶ ስለደረሰበት ሁኔታ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚለው የለውም። ጳውሎስ ከተፈታ በኋላ ቲቶ ከጳውሎስ ጋር በመተባበር አራተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው የሚባለውን አገልግሎት ያከናወነ ይመስላል። ጳውሎስና ቲቶ ወደ ቀርጤስ ከተማ ሲደርሱ፥ ጳውሎስ ቲቶ በዚያ ሆኖ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲያደራጅ አደረገ። ከዚያ ጳውሎስ ወደ ኤፌሶንና መቄዶኒያ ተጓዘ። በዚህም ጊዜ ቲቶ የሚደርስበትን ተቃውሞ ለማሸነፍ ሥልጣኑን እንዲጠቀምና እውነትን እንዲያስተምር አሳስቧታል። በኋላ ግን ሌሎች መሪዎች በቲቶ እግር በመተካታቸው በኒቃፖሊስ ከጳውሎስ ጋር ሊገናኝ ችሏል። ኒቃፖሊስ ከግሪክ በምዕራባዊ ዳርቻ የምትገኝ ከተማ ነበረች። በኋላ በደልማጢያ (ያሁኗ ዩጎዝላቪያ) እንዲያገለግል የተጠየቀ ይመስላል። ጳውሎስ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ሁለተኛውን የጢሞቴዎስ መልእክት በጻፈበት ወቅት ቲቶ በዚያች ከተማ ውስጥ ያገለግል ነበር። አንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚለው፥ ከዚያ በኋላ ቲቶ ወደ ቀርጤስ ተመልሶ ጳጳስ ሆኗል። በዚህም በደሴቲቱ ውስጥ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት የማስተባበሩን ተግባር አከናውኗል።

የቀርጤስ ደሴት የምትገኘው ከግሪክ በስተደቡብ ነበር። (ከመጽሐፉ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት።) ይህቺ ደሴት 350 ኪ.ሜትሮች ያህል ርዝመት ያላት ሰፊ ስፍራ ነበረች። ቤተ ክርስቲያን በዚህች ደሴት ውስጥ እንዴት እንደ ተመሠረተች የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የገለጸው ነገር የለም። በበዐል ኀምሳ በክርስቶስ ያመኑ አንዳንድ የቀርጤስ ሰዎች እንደነበሩ ይናገራል (የሐዋ. 2፡11)። ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ ወደ ሮም በሚሄድበት ጊዜ የቀርጤስን ደሴት ጎብኝቷታል። በዚህ ጊዜ በዚህች ከተማ ውስጥ የስብከት አገልግሎት ለመስጠት የተፈቀደለት መሆኑ አልተገለጸም። ነገር ግን ይህን ለማድረግ ፈቃድ ያገኘ አይመስልም። ጳውሎስ ከመጀመሪያው የሮም እሥራት ከተፈታ በኋላ፥ ወደ ቀርጤስ ቲመልሶ አገልግሏል። ሌሎችን አካባቢዎች ለመጎብኘት በፈለገ ጊዜ፥ ቲቶ በዚያ ሆኖ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲያደራጅ አድርጓል። ስለሆነም ጳውሎስና ቲቶ ይህችን ቤተ ክርስቲያን በጋራ የመሠረታት ይመስላል። ቲቶ አመራሩን የማደራጀቱን ተግባር ለብቻው ተወጥቷል። ምናልባትም ቤተ ክርስቲያኒቱ አዲስና ብዙ ምእመናን ያልነበሯት በመሆኑ ይመስላል ዲያቆናትን መሾም አላስፈለገም።

የቀርጤስ ሰዎች ወደ ደሴቲቱ ከመጡት ጥንታዊያን ቀርጤላውያንና ግሪኮች የተወለዱ ነበሩ። (የብሉይ ኪዳን ፍልስጤሞች የመነጩት ከዚህ ነው።) የቀርጤስ ሰዎች የሠለጠኑ ሰዎች ሳይሆኑ፥ በጭካኔአቸው፥ ታማኞች ባለመሆናቸውና በስንፍናቸው ይታወቁ ነበር። በዚህ ስፍራ ወንጌልን በጽናት መመሥረቱና መሪዎችን ማስመረጡ የቲቶ ኃላፊነት ነበር። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ የአማኞቹን ሕይወት ሊለውጥና የእግዚአብሔር ልጆች እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባ የሚያሳዩ ሞዴሎች ሊሆኑ እንደሚገባ አስረድቷል።

ቲቶ የተጻፈበት ዘመንና ቦታ

እንደ 1ኛ ጢሞቴዎስ ሁሉ የቲቶ መልእክት ስለተጻፈበትም ጊዜ ምሁራን የተለያዩ አመለካከቶች አሏቸው። ይህም ምሁራኑ ጳውሎስ ከሐዋርያት ሥራ 28 በኋላ ከእስራት ተፈትቷል ወይም አልተፈታም ለሚለው ጥያቄ በሚሰጡት መልስ ላይ የሚወሰን ነው። ጳውሎስ ከእስራት አልተፈታም የሚሉ ወገኖች የቲቶ መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ በ64 ዓ.ም ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ነው ይላሉ። አንደኛው አመለካከት ጳውሎስ በሦስተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው መጨረሻ ላይ ወደ ኢየሩሳሌም በሚሄድበት ወቅት ቲቶን ወደ ቀርጤስ እንደላከው ያስረዳል። ጳውሎስ በ57 ዓ.ም አካባቢ ከኢየሩሳሌም ሆኖ የቲቶን መልእክት ጻፈ። በዚህም መልእክቱ ቲቶ በቀርጤስ የተመሠረቱትን አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደሚያደራጅ መመሪያዎችን ሰጥቶታል። የበለጠ ትክክል የሚመስለው ግን ይህ መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ ከመጀመሪያ እሥራቱ ከተፈታ በኋላ እና ለሁለተኛ ጊዜ ከመታሰሩ በፊት ነው የሚለው ይመስላል። ጳውሎስ በሁለተኛው እስራቱ ወቅት የሞት ፍርድ ተፈርዶበት በ67 ዓ.ም እንደተገደለ ይታወቃል።

ጳውሎስ የቲቶን መልእክት በጻፈ ጊዜ የት እንደነበረ በእርግጠኛነት ለመናገር አንችልም። ብዙ ምሁራን ጳውሎስ በዚህ ጊዜ ቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ እንደነበረና ወደ ኒቃፖሊስ ለመሄድ እያቀደ መሆኑን ይናገራሉ (ቲቶ 3፡12)። (ኒቃፖሊስን የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ኒቆፖሊዮን ሲል ይጠራል።) ጳውሎስ የቀርጤስን ቤተ ክርስቲያን ሊመሩ የሚችሉ መልካም መሪዎች እየመጡ መሆናቸውን በመገንዘብ፥ ወደ ኒቃፖሊስ መጥቶ ከእርሱ ጋር እንዲገናኝ ቲቶን ጠየቀው። ኒቃፖሊስ ከቆሮንቶስ በስተሰሜን ምዕራብ 200 ኪ.ሜትሮች ርቃ የምትገኝ የወደብ ከተማ ነበረች። ምናልባትም ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው ለሁለተኛ ጊዜ ከመታሰሩ ጥቂት ቀደም ብሎ በ66 ዓ.ም አካባቢ ሳይሆን አይቀርም። የቲቶ መልእክት ከ1ኛ ጢሞቴዎስ አያሌ ወራት ቀደም ብሎ የተጻፈ ይመስላል።

የቲቶ መጽሐፍ ዓላማ

<u>የመጀመሪያው ዓላማ፡</u> ቲቶ በቀርጤስ ቤተ ክርስቲያን እንዲጉ እንደሚያደራጅ መግለጽ። ጳውሎስ ቲቶ መሪዎችን እንዲመርጥና አማኞች ደግሞ እምነታቸውን የሚያንጸባርቅ ሕይወት እንዲኖሩ ያበረታታቸው ዘንድ ይህን መልእክት ጽፎአል። ቲቶ ከጳውሎስ የተቀበለው አገልግሎት አስቸጋሪ ነበር። ቤተ ክርስቲያኒቱ በቅርብ ጊዜ የተመሠረተች አዲስ ነበረች። ይህ ጢሞቴዎስ በሚገባ በተደራጀች የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚያበረክተው አገልግሎት የተለየ ነበር። የቀርጤስ ሰዎች ያልተማሩ፥ ውሸታሞች፥ የማይታመኑ፥ ለመብላት ብቻ የሚኖሩ፥ ሰነፎች፥ ወዘተ... በመሆናቸው ባሕሪያቸው በጣም አስቸጋሪ ነበር። ጳውሎስ በክርስቶስ ላይ ያለን እምነት ባሕሪያችንን መለወጥ እንዳለበት አጽንኦት ሰጥቶ የሚናገረው ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። ይህ በተለይ ለመሪዎች እጅግ አስፈላጊ ነው።

ይህም እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳንን ሕዝብ የጸኑትን አይሁዶች ብቻ በወንጌል ለመለወጥ አለመፈለጉን ያሳያል። እንደ ግሪኮች ያሉትን የሠለጠኑ ሕዝቦች ብቻም አልነበረም የሚፈልገው፥ ላልተማሩና ብዙ ሕዝብ የማይሰብ ባህል ላላቸው ሕዝቦችም ይገደዋል። እግዚአብሔር ለቀርጤስ ሕዝብ የሚገደው ከሆነ፥ ለዘላኖች፥ ሸክላ ሠሪዎች፥ ብረት ቀጥቃጮች፥ እንዲሁም በዓለም በየትኛውም ስፍራ ለሚኖር ሕዝብ እንደሚገደው ግልጽ ነው። ቤተ ክርስቲያን የተናቁ ናቸው ብላ የምታስባቸውን የሕዝብ ክፍሎች በወንጌል ለመድረስ በማትፈልግበት ጊዜ የምእመኖቿ የክርስቶስን ምሳሌነት እየተከተሉ አለመሆናቸውን መመልከት ይችላል። ለሰዎች ሁሉ የሚራራ የእግዚአብሔርም ልብ እንደሌላቸው ግልጽ ነው።

ወንጌሉ የተለያየ ባህል ወዳሏቸው ሕዝቦች የሚደርስበት ጊዜ፥ አማኞቹ እግዚአብሔርን የማያስከብረውን የባህላቸውን ክፍል መከተል አይኖርባቸውም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የባህሎች ሁሉ ዳኛ ሆኖ መቀመጥ ይኖርበታል። የየትኛውም ባህል ተከታዮች የሆኑ ሕዝቦች እግዚአብሔር ከባህላቸው ውስጥ የትኛው እርሱን እንደማያስከብረው እንዲያሳያቸው ሊጠይቁትና ይህንኑ ባህሪ ሊለውጡት ይገባል። አንድ ባህል ውሸት፥ አለመተማመንና ስርቆት ተገቢ እንደሆነ ቢያስተምር፥ የእግዚአብሔር ቃል እነዚህን የባህሉን ክፍሎች አማኞች ሊለውጡ እንደሚገባ ያስገነዝባል።

ነገር ግን ወንጌል ሊለውጠው የሚገባውን እንዳለ መተው የሚገባውን የባህል ክፍል በምንገመግምበት ጊዜ በጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። ጳውሎስ ያልሠለጠኑትን የቀርጤስ ሰዎች በሚያስተምርበት ጊዜ፥ በየትኛውም ስፍራ የግሪክን ባህል እንዲከተሉ፥ ትምህርት እንዲከታተሉ፥ የተወሰነ የአለባበስ ስልት እንዲይዙ ወይም የተወሰነ ቋንቋ እንዲማሩ አልጠየቃቸውም። ከቃሉ ጋር በግልጽ በሚጣረሱ አካባቢዎች ካልሆነ በስተቀር፥ እግዚአብሔር ሕዝቦች ባህላቸውን እንዲከተሉ ይፈቅዳል። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች በሙሉ በአንድ ቋንቋ እንደሚያመልኩ፥ የተወሰነ የአለባበስ ስልት እንደሚከተሉ፥ ኳየሮች እንደሚኖሩዋቸው፥ በቆርቆሮ ቤቶች ውስጥ እንደሚጸልዩ፥ እንደሚማሩ፥ የምዕራባውያንን ልብሶች እንደሚለብሱ፥ ወዘተ... እናስባለን። አንዳንድ ወንጌላውያን ዘላኖች ይህንኑ የባህላቸውን ክፍሎች እንዲቀይሩ በተሳሳተ መንገድ ያስተምራሉ። ወንጌላውያን የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ማስተማር ሰዎች የገዛ ባህላቸውን ትተው የእነርሱን ባህሎች እንዲከተሉ ያስተምራሉ። ይህ ቅኝ ገዢዎች ኋላ ቀር ባህል ያላቸውን ሰዎች የባእድ አገሮችን ባህሎች እንዲከተሉ ካስገደዱበት መንገድ ጋር የሚመሳሰል የተሳሳተ አመለካከት ነው። ወንጌላውያን መቃወም ያለባቸው ከእግዚአብሔር ጋር የሚቃረኑትን ባህሎች ብቻ ነው። ይህንኑም የሚያደርጉት እንደ ጳውሎስ እግዚአብሔር ክርስቲያኖች የሚጠብቃቸውን አዎንታዊ የባህሪ ለውጦች በማመልከት ሊሆን ይገባል። ሰዎች እንዴት ሊለወጡ እንደሚገባ የሚዘረዝሩ ሕጎችን ልንሰጣቸው አንችልም። ይህ ወንጌሉን የሰናይ ምግባራት ሃይማኖት ከማድረጉም በላይ፥ ባህላችንን በሌሎች ሰዎች ባህል ላይ እንድንጭን ያበረታታናል። ጳውሎስ

ለአይሁዶች ወንጌልን ለማካፈል በፈለገ ጊዜ አይሁዳዊ ሆኖ እንደቀረበ ገልጾአል። ይህንን ያደረገው እንደ ዕብራውያን ሰዎች በመልበስ፥ ቋንቋቸውን በመናገርና ልክ እንደ እነርሱ በማምለክ ነበር። ለአይሁዶች ወንጌልን በሰበከ ጊዜ የአይሁዶችን ባህል ተከትሏል። የግሪክን ቋንቋ በመጠቀም፥ እንደ ግሪኮች በመልበስና እንደ ግሪኮች በማምለክ አገልግሎቱን ተወጥቷል። (በዚህ ጊዜ ግን ጳውሎስ እግዚአብሔር በግልጽ የከለከለውን የጣዖት አምልኮ አልተከተለም።) አይሁዶች ግሪኮች እንዲሆኑ ወይም ግሪኮች አይሁዶች እንዲሆኑ ከማስገደድ ይልቅ፥ ወንጌሉ የሚሰሙትን ይማርክ ዘንድ መልእክቱን ከሰሚዎቹ ባህል ጋር በሚጣጣም መልኩ ለማቅረብ መጣሩ ተገቢ ይሆናል (1ኛ ቆሮ. 9፡19–23)።

22ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የእግዚአብሔር ቃል ከሚያስተምረው በግልጽ የሚጣረሱትን የባህልህን ክፍሎች በምሳሌነት ዘርዝር። አብዛኞቹ አማኞች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ይከተላሉ ወይስ እንደ ዓለማውያን በመኖር ተግባራቸው የባህላቸው ውጤት መሆኑን ለማመሃኛነት ያቃርባሉ? ለ) ከእግዚአብሔር ጋር በግልጽ የሚቃረኑትን የሌሎች ባህሎች ገጽታዎች ዘርዝር። ብዙውን ጊዜ ከራሳችን ይልቅ የሌሎችን ባህሎች ችግሮች መመልከት የሚቀልለን ለምንድን ነው? ሐ) ሚሲዮናውያን ወይም ከሌሎች ባህሎች የመጡ ወንጌላውያን ሰዎች ክርስቲያን ለመሆን ከፈለጉ ባህላቸውን መለወጥ እንዳለባቸው የሚያስተምሩበትን ሁኔታ ግለጽ። መ) ይህ አደገኛና እግዚአብሔር ከሚፈልገው ሁኔታ ጋር የማይጣጣመው ለምንድን ነው? ሠ) በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ የተናቁ ባህሎች ዘርዝር። ብዙ ሰዎች ለእነዚህ ባህሎች ምን ዓይነት አመለካከቶች አሏቸው? ለእነዚህ ሰዎች ወንጌሉን ለመመስከርና በእኩልነት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ ለማድረግ አንተ፥ ቤተ ክርስቲያንህ ወይም ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ምን እያደረጉ ናቸው?

ሁለተኛ ዓላማ፡– ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈው ለቲቶ ቢሆንም፥ ዓላማው የቀርጤስ አማኞች እንደ እግዚአብሔር ልጆች እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው ማስተማር ነው። ጳውሎስ ቲቶ የእርሱ ተወካይ እንደሆነና የሚሰጣቸውን መልእክት ሊቀበሉ እንደሚገባ ለአማኞቹ ያስረዳል።

ሦስተኛ ዓላማ፡– እግዚአብሔርን የምታከብር ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን ለማደራጀት ምን ዓይነት ዐበይት ነገሮች እንደሚያስፈልጉ ለጢሞቴዎስና ለሌሎችም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለማስተማር። ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን የመገንባቱ ተግባር በድንገት የሚከሰት ሳይሆን፥ ሁሉንም የዕድሜ ክልሎች በጥልቀት ማስተማርን የሚጠይቅ ነው።

አራተኛ ዓላማ፡– ጢሞቴዎስና የቀርጤስ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሐሰተኛ ትምህርቶች እንደሚቋቋሙ ለመምከር። በቀርጤስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ሐሰተኛ ትምህርት ጠቅላላ ቤተሰቦችን እያወከ ያለ ይመስላል (ቲቶ 1፡11)። ቤተ ክርስቲያኒቱን እያጠቃ ያለው ሐሰተኛ ትምህርት ከአይሁዳውያን ክርስቲያኖች የመጣ ነበር። (ከተገረዙት ወገን፥ ቲቶ 1፡10፤ 14)። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ በመግለጽ የብሉይ ኪዳንን ሕግ መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን አስተምሯል። ተግባራቸው ግን ጭራሽ እግዚአብሔርን የማያውቁ መሆናቸውን አጋልጧል (ቲቶ 1፡10–16፥ 3፡9)።

አምስተኛ ዓላማ፦ በክርስቶስ ላይ የተጣለ እምነት በመልካም ባሕሪ ራሱን እንደሚገልጽ ለማሳየት። አማኞች በክርስቶስ አምናለሁ እያሉ አለማመናቸውን በሚያሳብቅ አኳኋን ሊመላለሱ ይችላሉ (ቲቶ 1፡16)። የአማኞች ባሕሪና ተግባር በክርስቶስ ማመን ሕይወታቸው ያመጣውን ለውጥ በሚያሳይ መልኩ መለወጥ አለበት። አዲስ ፍጥረት በተለወጠ ሕይወት ራሱን ያሳያል።

23ኛ ጥያቄ፦ እነዚህ ትምህርቶች ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

የቲቶ ልዩ ባሕርያት

1) ቲቶ ስለ ክርስቶስ አምላክነት ግልጽ የሆነ ትምህርት ያቀርባል። በቲቶ መልእክት ውስጥ ክርስቶስ ታላቅ አምላክና አዳኝ ተብሎ ተጠቅሷል። ይህም ብዙውን ጊዜ ለእግዚአብሔር አብ የሚያገለግል ስያሜ ነው (ቲቶ 2፡13)።

2) የቲቶ መጽሐፍ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ የሚገኙትን አብዛኞቹን ጉዳዮች ይዳስሳል። የሽማግሌዎች ምርጫ፥ የሴቶችና የባሪያዎች ሚና፥ እንዲሁም ሐሰተኛ ትምህርቶችን መከላከል የሚሉ ዐቢይ ነጥቦች በሁለቱም መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ።

3) ቲቶ ከማናቸውም የጳውሎስ መልእክቶች በላይ ከተገቢው እምነትና መንፈሳዊ ባሕሪ መካከል ያለውን ግንኙነት በግልጽ ያሳያል። ከተገለጹት ሐረጎች መካከል «መልካም ባሕሪ» የሚለው ይገኝበታል። ይህም የክርስቶስን ስም የሚጠሩ ሰዎች እንደ እግዚአብሔር ልጆች ሊመላለሱ እንደሚገባ ያሳያል።

4) ቲቶ ወንጌል ምን እንደሆነ ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል። በቲቶ 2፡11-13 የጸጋው ወንጌል ምን ዓይነት ውጤቶችን እንደሚያስከትል ተገልጾአል። ወንጌል፥ መንፈሳዊ ያልሆኑትን ባሕሪዎች እንዳንከተልና መንፈሳዊ አኗኗርን እንድንሻ ያደርገናል። በቲቶ 3፡4-8፥ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ወደሚያምኑት ሕይወት ስለሚያመጣቸው እንደ ምሕረት፥ ደኅንነትና ተሐድሶ በመሳሰሉት ነገሮች ላይ ያተኩራል። አሁንም ጳውሎስ ትክክለኛ እምነት እንዴት ወደ መንፈሳዊ አኗኗር እንደሚመራ አጽንኦት ሰጥቶ ገልጾአል።

የቲቶ አስተዋጽኦ

ይህ የቲቶ መልእክት አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በአዲስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያደራጃቸው ስለሚገቡ የተለያዩ ነገሮች የሚናገር ተግባራዊ መልእክት ነው። በመሆኑም፥ እነዚህ ነገሮች መሪዎች ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት የሚጠቁመባቸውን መሠረታዊ እውነቶች ያቀርባሉ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ አዲሷን ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደሚያደራጅ በሚመክርበት ጊዜ ግልጽ አስተዋጽኦ ከመከተል ይልቅ ከርእሰ ጉዳይ ወደ ርእሰ ጉዳይ እያለፈ የተለያዩ ትምህርቶችን ያቀርባል። የቲቶ መልእክት አጠቃላይ መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል፦

1. ብቃት ያላቸውን መሪዎች መሾም (ቲቶ 1፡1-9)

ሐ) መግቢያ (ቲቶ 1፡1–4)

ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተገቢውን አመራር መመሥረት (ቲቶ 1፡5–9)።

2. የሐሰት ትምህርቶችን ስለመከላከል (ቲቶ 1፡10–16)

3. ለሁሉም የዕድሜ ክፍሎች ግልጽ ትምህርት በማቅረብ ቤተ ክርስቲያንን ማጠናከር (ቲቶ 2፡1–10)

ሀ) አረጋውያንን ማስተማር (ቲቶ 2፡1–2)

ለ) አረጋውያን ሴቶችን ማስተማር (ቲቶ 2፡3–5)

ሐ) ወጣት ወንዶችን ማስተማር (ቲቶ 2፡6–8)

መ) ባሮችን ማስተማር (ቲቶ 2፡9–10)

4. የጸጋው ወንጌል የተለወጠ አኗኗርን እንደሚያስከትል ማስተማር (ቲቶ 2፡11–3፡15)

ሀ) ወንጌል አማኞች መንፈሳዊ ያልሆኑትን ልምምዶች እንዳይከተሉ ያደርጋል (ቲቶ 2፡11–3፡8)።

ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ጋር ማቆሚያ የሌለው ክርክር መግጠም የለበትም (ቲቶ 3፡9–11)።

ሐ) ድምዳሜ (ቲቶ 3፡12–15)

አራተኛ ቀን ቲቶ 1–3

ግርማዊ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገና ተመርቆ መውጣቱ ነበር። ራቅ ባለ ስፍራ በሚገኙ ጎሳዎች መካከል አብያተ ክርስቲያናት እንዲመሠርት በቤተ ክርስቲያን ተልኮ ሄደ። ግርማዊ አንድ ወንጌላዊ ምን ማድረግ እንዳለበት በቂ ሥልጠና ሳያገኝና አብሮት የሚሠራ ልምድ ያካበተ አገልጋይ ከአጠገቡ ሳይቆም ወደ አዲሱ አካባቢ ተጓዘ። እግዚአብሔር ስለባረከው ብዙም ሳይቆይ ሰዎች በክርስቶስ ማመን ጀመሩ። ከዚያ በኋላ ግን ግርማዊ፥ «አሁን ምንድን ነው የማደርገው? እነዚህ ክርስቲያኖች ከአማኝነት ወደ በሳል ክርስቲያንነት የሚለወጡት እንዴት ነው?» ሲል አሰበ። ግራ ተጋብቶ በነበረበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ የግርማዊን ቀልብ ወደ ቲቶ መልእክት መለሰው።

24ኛ ጥያቄ፡– ቲቶ 1–3 አንብብ። ቲቶ ግርማዊ አዳዲስ አማኞችን በጤናማ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሳል ክርስቲያኖች አድርጎ ለማደራጀት ምን ሊያደርግ እንደሚገባ ይመክረዋል? በክፍሉ ውስጥ የተጠቀሱትን ጠቃሚ ነጥቦች ዘርዝር።

ጥሩ ወጥ ለመሥራት ጥራት ያላቸውን ቅመሞች በተገቢው መጠን መጨመር እንደሚያስፈልግ ሁሉ፥ ጤናማ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረትም አንዳንድ ነገሮች ሊካተቱ ይገባል። ቲቶ የሚያገለግላትና በቀርጤስ ደሴት የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን አዲስና ብዙም መንፈሳዊነት የማይታይባት ነበረች። ጳውሎስ ቲቶ ይህቺን ያልበሰለች ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ወደምታስከብር በሳል ቤተ ክርስቲያንነት እንዲለውጥ አደፋፍሮታል። ጳውሎስ ለዚህ ተግባር የሚከተሉትን ነገሮች እንዲያደርግ ያበረታታዋል። ሀ) መንፈሳዊ አመራር፥ ለ)

የሐሰት ትምህርቶችን መከላከል፥ ሐ) በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ባሕሪያቸውንና አኗኗራቸውን የሚለውጥ ጥረት ያለው የትምህርት ፕሮግራም መከታተልና መ) ወንጌሉን በግልጽ መረዳት። ደኅንነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በማመን መሆኑንና የዳኑ ሰዎች ግን እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ መመላለስ እንዳለባቸው ማወቅ ያስፈልጋቸው ነበር።

ብቃት ያላቸውን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሾም (ቲቶ 1፡1–19)።

1) መግቢያ (ቲቶ 1፡1–4)

ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር ከእርሱ የሚፈልገውን ነገር በትክክል ያውቅ ነበር። ጳውሎስ ሕይወቱን በሙሉ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ የሚኖር ባሪያ ነበር። ምንም እንኳ ይህ እስራትና ሞትን ቢያስከትልበትም፥ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የቆረጠ አገልጋይ ነበር። እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌሉን እንዲሰብክ የሾመው ሐዋርያ ነበር። ወንጌሉ እግዚአብሔር ለጳውሎስ የገለጸውን የማይለወጥ እውነት የያዘ ነበር። ሰዎች የዘላለምን ሕይወት የሚያገኙት እግዚአብሔር የገለጠው እውነት ሲሰበክና ይህንኑ እውነት ሲያምኑ ነው። ነገር ግን ሕይወትን የማይለወጥ እውነት መስበኩ ብቻ በቂ አይደለም። ወንጌሉ የተለወጠ ሕይወት በማስከተል ሰዎች መንፈሳዊ አኗኗር እንዲከተሉ ያደርጋልና። ወንጌሉ የሚቀርበው በሚከተለው ቅደም ተከተል ነው። 1) የእግዚአብሔር እውነት ይሰበካል፥ 2) ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ያምናሉ፥ 3) ወንጌሉን የሚያንጸባርቅ ሕይወት ይኖሩ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማኞች አኗኗራቸውን ይቀይራሉ። ይህንን ቅደም ተከተል ስንቀይርና በቀዳሚነት ሰዎች ከደኅንነት በኋላ ሊያሳዩ በሚገቧቸው ለውጦች ላይ ስናተኩር፥ ብዙውን ጊዜ ወንጌሉ ይለወጥና ሰዎች ደኅንነትን ለማግኘት መልካም ተግባር ማከናወን እንዳለባቸው ያስባሉ።

2) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተገቢውን አመራር ማደራጀት (ቲቶ 1፡5–9)

ምናልባትም ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት የሚያደርገው እጅግ ወሳኙ ነገር ትክክለኛ መሪዎች መመረጣቸው ይሆናል። ብዙውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ደካማ የምትሆነውን ሀ) መሪዎች በእምነታቸው ደካማ ሲሆኑ፥ ለ) የመንፈሳዊነት ሞዴሎች ሆነው ባለመመለሳቸው፥ ወይም ሐ) አማኞችን በትክክል ባለማስተማራቸው ሊሆን ይችላል።

25ኛ ጥያቄ፡– እነዚህ ሦስት ነገሮች የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ሲገድሉ የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ።

ጳውሎስ ቲቶ በአዲሲቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያደርግ የፈለገው የመጀመሪያው ነገር ትክክለኛ መሪዎችን መሾም ነበር። ቲቶ በዚህች አዲስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎችን ለመምረጥ ምን ዓይነት የመሪነት ብቃቶችን መመዘኛ አድርጎ መጠቀም ያስፈልገው ነበር? ጳውሎስ ለቲቶ የዘረዘራቸው የብቃት መመዘኛዎች በአብዛኛው ለጢሞቴዎስ የዘረዘራቸው

ናቸው (1ኛ ጢሞ. 3፡1–13)። ለመሪዎች የሚያስፈልጉ የብቃት መመዘኛዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ።

1. ነቀፋ የሌለበት ይህም በባሕሪው፥ ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነትና ከገንዘብ ጋር ባለው ግንኙነት፥ ወዘተ... ያጠቃልላል።

2. የአንዲት ሚስት ባል፥ ብዙ ሚስቶች የሌሉት

3. የሚያምሩ ልጆችና በሥርዓት የተያዘ ቤተሰብ ያለው መሪ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ ምን መምሰል እንዳለበት በሞዴልነት የሚያሳይ አገልጋይ ነው። መሪነቱን የማስተማር ብቃቱ በልጆቹ ባሕሪና ተግባር መታየት ይኖርበታል።

4. ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ተገቢውን ባሕሪ ማንጸባረቅ አለበት። የማይጠጣ፥ የማይበላጭ፥ የማይጣላና እንግዳ ተቀባይ መሆን ይኖርበታል።

5. የአልኮል መጠጦች ቁራኛ ያልሆነ

6. ለሀብትና ገንዘብ ትክክለኛ አመለካከት ያለው

7. መንፈሳዊ ባሕሪ ያለው፥ ራሱን የሚገዛ፥ ቀጥተኛ ሥነ ምግባራዊ ሕይወት የሚኖርና የተቀደሰ

8. እውነትን የሚያውቅ፥ የሚጠብቅና የሚያስተምር

26ኛ ጥያቄ፡– ሀ)ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚወድቁባቸው ብቃቶች የትኞቹ ናቸው? ለ) እነዚህ ብቃቶች በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ መንጸባረቃቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) በእነዚህ በቲቶ መልእክት ውስጥ ከተገለጡት በተጨማሪ ዛሬ ትኩረት የምንሰጣቸው ሌሎች የብቃት መመዘኛዎች የትኞቹ ናቸው? መ) የመሪ መንፈሳዊ ጥረት የቤተ ክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ ደረጃ ሊወስን የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ።

በ1ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ እንደተመለከትነው፥ ጳውሎስ አጽንኦት የሚሰጥባቸው ዐበይት የብቃት መመዘኛዎች የግለሰቡ ባሕሪና መንፈሳዊነት፥ ቤተሰባዊ ሕይወቱ፥ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለው ግንኙነትና እውነትን የማስተማር ብቃቱ ናቸው። ጳውሎስ ዛሬ አስፈላጊ ናቸው ብለን የምናስባቸውን እንደ የትምህርት ደረጃ፥ የጎላ ሥረ መሠረት፥ ሀብት፥ ወዘተ... አይጠቅስም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜ፥ በአመዛኙ የችግሩ ምንጭ የሚውለው ከመሪዎች ላይ ነው። በመሪዎች መካከል ችግሮች የሚከሰቱት ደግሞ በአብዛኛው ጳውሎስ መሪዎችን ለመምረጥ መሠረታዊ አድርጎ የሚጠቅሳቸው ባሕርያት ስለሌሉአቸው ነው። ብዙውን ጊዜ በመሪዎች ላይ የምናጉረመርም ከሆነ ምናልባትም ችግሮቹ ራሳችን እንሆናለን። የምናገኘው የምንመርጠውን ነው። ምርጫችን በተሳሳተ መመዘኛ ላይ የተመሠረተ ከሆነ፥ የሚጨቁኑንን ወይም እንደ ፖለቲካ መሪዎች የሚያጉላሉንን መሪዎች እናጭዳለን። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛዎች ላይ ተመሥርተን ከመረጥን፥ እግዚአብሔርን የምታስከብር ቤተ ክርስቲያን ትኖረናለች።

ሐሰተኛ ትምህርቶችን መከላከል (ቲቶ 1፡10–16)

የቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን እኛ እንደምናስበው ፍጹም አልነበረችም። ምክንያቱም ልክ እንደ እኛው አብያተ ክርስቲያናቱ ከሐሰት ትምህርት ጋር ግብግብ ይፈጥሩ ነበር። በየትኛውም ዘመን ውስጥ በምትኖር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮች፥ ክፍፍሎችና ሐሰተኛ ትምህርቶች ከውስጥ ሊመነጩ፥ ከውጭ ደግሞ ስደት ሊመጣ ይችላል። ጳውሎስ ቲቶ ስለ ሐሰተኛ ትምህርት ጥንቃቄ እንዲያደርግ ያሳስበዋል። ቀርጤስ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ብትሆንም፥ ሐሰተኛ ትምህርቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይዛመዱ ትምህርቶች በማቅረብ ላይ ነበሩ። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም መሪዎች ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል? እውነትን በማስተማር ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ዝም ማሰኘት ይኖርባቸዋል። በጳውሎስ ዘመን፥ ዋንኛው የሐሰት ትምህርት የመነጨው ክርስቲያኖች ነን ከሚሉ አይሁዶች ነበር። እነዚህ ሰዎች ክርስቲያኖችን በእምነት ከሚገኝ ደኅንነት በሥራ ወደሚገኝ ደኅንነት (ግርዘት፥ የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት መጠበቅ፥ ወዘተ...) ለመለወጥ ፈልገው ነበር። አሁንም ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዐበይት ኃላፊነቶች አንዱ ቤተ ክርስቲያንን ከሐሰተኛ አስተማሪዎች መጠበቅ መሆኑን እንመለከታለን። ይህንንም ለማድረግ፥ እውነትን ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ሁሉንም የዕድሜ ክፍሎች በማስተማር ቤተ ክርስቲያንን ማጠናከር (ቲቶ 2፡1–10)

እውነትን ማስተማር በሁሉም የቤተ ክርስቲያን መሪ የብቃት መመዘኛዎች ዝርዝር ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እውነትን እንዲያስተምር ከተፈለገ አራት ነገሮች ያስፈልጉታል።

1. *መሪው ራሱ እውነትን ማወቅ ይኖርበታል።* የወንጌሉን መሠረታዊ እውነቶች የሚያውቅ መሪ ለቤተ ክርስቲያን አመራር ከሚያስፈልጉ ወሳኝ መመዘኛዎች አንዱ ይጎድለዋል። በግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ መጻሕፍትን በማንበብ፥ በቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፥ ትመማ፥ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብቶ በመማር፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እውነትን ማወቅ ይኖርባቸዋል።

2. *መሪ እውነትን በሚያንጸባርቅ መልኩ መመላለስ አለበት።* መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናው የአእምሮ ዕውቀት ለማግኘት ብቻ አይደለም። ነገር ግን የምንማራቸውን እውነቶች በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል።

3. *መሪ ለማስተማር የሚችል መሆን አለበት።* አንዳንድ ሰዎች እውነተኛና መንፈሳዊ የሆነውን ነገር ቢያውቁም፥ ለሌሎች የማስተማር ብቃት የላቸውም፥ ጳውሎስ ዋና አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማስተማር እስከሆነ ድረስ፥ መሪ የማስተማር ስጦታ ሊኖረው እንደሚገባ ያስገነዝባል። ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ከዐበይት መንፈሳዊ ስጦታዎች አንዱ ማስተማር እንደሆነ የሚያብራራው (1ኛ ቆሮ. 12፡28 አንብብ)።

4. *መሪ ለማስተማር ጊዜ መውሰድ አለበት።* ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎች ተግባራትን በማከናወን ራሳቸውን ስለሚያባክኑ ለማስተማሪያ የሚሆን ጊዜ የላቸውም። በዛሬው ዘመን ብዙ ሰዎች በቤተ

ክርስቲያን ውስጥ በአግባቡ ትምህርት አያገኙም። ይህም ሆኖ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምስት ወይም ከዚያ የሚበልጡ ሽማግሌዎች አሉ። እነዚህ ሽማግሌዎች ለአባሎቻቸው እውነትን የሚያስተምሩበትን መንገድ ማግኘት ይኖርባቸዋል። መሪዎች ምእመናቻቸውን ማስተማር ካላስፈለጋቸው፥ እግዚአብሔር የማስተማር ብቃት እንዲኖራቸው የሚጠይቀው ለምን ይሆን? የሚያሳዝነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብዛኞቹ ሽማግሌዎች በማስተማር አገልግሎት ላይ የማይሳተፉ መሆናቸው ነው። ወይም ደግሞ የሚያስተምሩት እሑድ ጧት ብቻ ይሆናል። ጳውሎስ ቲቶ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተለያዩ ቡድኖች ትኩረት በመስጠት ፍላጎታቸውን የሚያሟላ ትምህርት እንዲሰጣቸው ያብራራል።

27ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች የማስተማርን አገልግሎት በአግባቡ የማይወጡት በቀዳሚነት እነዚህ አራት ምክንያቶች ከየትኛው የተነሣ ነው? ለ) ይህን ሁኔታ ለመለወጥ ምን ሊደረግ ይገባል?

ጳውሎስ የተለያዩ ወካይ ቡድኖችን በመዘርዝር ሁሉም ዓይነት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መማር እንዳለባቸው ያስገነዝባል።

1. አረጋውያንን ማስተማር (ቲቶ 2፡1-2)። ጳውሎስ ቲቶ ጤናማ ትምህርትን እንዲያስተምር ያሳሰበዋል። ጳውሎስ ይህን ሲል የመጽሐፍ ቅዱስን ዐበይት እውነቶች ማለቱ ነው። ጳውሎስ ቲቶ ለአረጋውያን አማኞች የማይለወጠውን የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ማስተማር እንዳለበት ያስገነዝበዋል። ለመሆኑ አረጋውያን የሚማሩት ለምንድን ነው? ጳውሎስ አረጋውያን ባሕሪያቸውን ለመለወጥ የእግዚአብሔርን ቃል መማር እንዳለባቸው ያስረዳሉ። ውሸታሞች፥ የማይታመኑና ሰነፎች ከመሆን ይልቅ ጭምቶች፥ ሊከበሩ የሚገባቸው፥ ራሳቸውን የሚገዙ፥ በእምነት፥ በፍቅርና በትዕግሥት የተሞሉ መሆን ያስፈልጋቸው ነበር። እነዚህ አረጋውያን በባህላቸው ከታወቀው ሁኔታ የተለየ ሕይወት መምራት ያስፈልጋቸው ነበር።

2. አሮጊቶች (ቲቶ 2፡3-5)። ቲቶ አሮጊቶችንም ማስተማር ያስፈልገው ነበር። አሁንም ጳውሎስ ትኩረት ያደረገው በባሕሪና ተግባር ለውጥ ላይ ነው። በአሉታዊ ጎኑ፥ አሮጊት ሴቶች አንደበታቸውን በመግዛት ሰዎችን ከመሳደብ ወይም ከማማት መቆጠብ ያስፈልጋቸው ነበር። ለስካር እንዳይጋለጡ የሚጠጡትን መጠን መወሰን ያስፈልጋቸው ነበር። በአዎንታዊ ጎኑ፥ በአኗኗራቸው እግዚአብሔርን ማስከበር ያስፈልጋቸዋል። በአኗኗራቸውና በትምህርታቸው ለወጣት ሴቶች አዎንታዊ ተጽዕኖ ማሳደር ያስፈልጋቸዋል። አሮጊቶች ወጣት ሴቶች ራሳቸውን እንዲገዙ፥ ንጹሕ ሕይወት እንዲመሩ፥ ደጎች እንዲሆኑና መንፈሳዊ ቤቶች እንዲኖሯቸው፥ እንዲሁም ባሎቻቸውን እንዲያከብሩ ማስተማር ያስፈልጋቸዋል። ይህም በተለወጠ ሕይወታቸው እግዚአብሔርን ከማሰደብ ይልቅ እንዲያስከብሩ ያስችላቸዋል።

3. ወጣት ወንዶች (ቲቶ 2፡6-8)። ቲቶ እንደ ጢሞቴዎስ ወጣት የነበረ ይመስላል። የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ መሆኑ መጠን፥ የዕድሜ እኩያዎቹ ለሆኑት ሰዎችም ኃላፊነት ነበረበት። ለእነዚህ ወጣት ወንዶች የሚያስተምረው ዋንኛ ባሕሪ ራስን ስለመግዛት ነበር። ወጣቶች ምኞታቸው፥ አሳባቸውና ፍላጎታቸው እንዲቆጣጠራቸው ከመፍቀድ ይልቅ በእግዚአብሔር ፈቃድ

መመላለስ ያስፈልጋቸው ነበር። ለመሆኑ ወጣቶችንና ሌሎችንም የሚያስተምረው እንዴት ነው? በእነዚህ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የክፍል ውስጥ ትምህርት በመስጠት ይሆን? አይደለም። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ በሁሉም የዕድሜ ክልል ላሉት ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወቱ ምሳሌ በመሆን እንዲያስተምራቸው ያሳስባል። ሕይወቱ እውነተኛነትን፥ ተገቢ ንግግርን፥ መንፈሳዊነትን፥ ወዘተ... ማሳየት ነበረበት።

28ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ጳውሎስ በዚህ የአረጋውያን፥ የአሮጊቶች፥ የወጣቶች ዝርዝር ውስጥ ቢያንስ ሦስት ጊዜ ራስን ስለመግዛት ገልጾአል። ይህ ባሕሪ ለሁሉም የዕድሜ ክፍሎች አስፈላጊ የሆነው ለምን ይመስልሃል? ጳውሎስ ቲቶ መንፈሳዊ ባሕሪን በሞዴልነት ለሰዎች እንዲያሳይ የጠየቀው ለምንድን ነው? ሐ) በሕይወትህ የሚያስቸግሩህ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው? እነዚህ ባሕርያት በሕይወትህ ውስጥ እንዲታዩ ምን እያደረግክ ነው? መ) በቤተ ክርስቲያንህ እነዚህን እውነቶች እንዴት እያስተማርክ ነው?

---

4. ባሮች (ቲቶ 2፡9–10።) ጳውሎስ በመጨረሻ፥ ለባሮችም (ሠራተኞች) የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር እንደሚያስፈልግ ይናገራል። በጌቶቻቸው ሥር የሚተዳደሩ አማኝ ባሮች በአግባቡ ባይያዙም ምሳሌያዊ ሕይወት መኖር ያስፈልጋቸው ነበር። ጌቶቻቸውን ለመታዘዝና ለማስደሰት መጣር፥ ታማኞችና እምነት የሚጣልባቸው መሆን ያስፈልጋቸው ነበር። ይህ ክርስትናን ያስከብር ነበር። አጭበርባሪዎች፥ ሰነፎች፥ ሌቦች፥ የማይታዘዙ ወይም ተጨቃጫቂዎች የሆኑ እንደሆነ የክርስቶስን ስም ያሰድባሉ።

የጸጋው ወንጌል የተለወጠ አኗኗርን እንደሚያካትት ማስተማር (ቲቶ 2፡11–3፡15)

1. ወንጌል አማኞች መንፈሳዊ ያልሆኑትን ነገሮች እንዳያደርጉ ያስተምራል (ቲቶ 2፡11–3፡8)።

ለመንፈሳዊ ጉዞ ቁልፉ ሚዛናዊነት ነው። ብዙውን ጊዜ ሐሰተኛ ትምህርት ክርስቲያኖች በእምነታችንና በተግባራችን ሚዛናዊነት የጎደለው እርምጃ እንድንወስድ ይገፋፋናል። የሚዛናዊነት መዛባትና የተሳሳተ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሚገቡባቸው መንገዶች አንዱ ደኅንነትን ባገኘንበትና በምንመላለስበት መንገድ መካከል ባለው ግንኙነት ነው። የአዲስ ኪዳን ዋነኛ ትምህርት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መዳናችንን መግለጽ ነው። እርሱ ከጸጋው የተነሣ በነፃ የዘላለም ሕይወት ይሰጠናል። ምንም እንኳ ሰይጣን ሁልጊዜም ደኅንነትን ለማግኘት ወይም ያገኘነውን ደኅንነት ጠብቀን ለማቆየት መልካም መሆን ወይም መልካም ሥራ መሥራት እንዳለብን ለማሳሰብ ቢፈልግም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ደኅንነት ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ኃጢአት መሞቱን ባመንንበት ጊዜ በነፃ የምናገኘው ስጦታ መሆኑን ይናገራል።

ነገር ግን ይህም ትምህርት ሚዛናዊነቱን ሊያጣ ይችላል። የቀርጤስ አማኞች፥ «ደኅንነት የሚገኘው በእምነት ብቻ ከሆነ፥ በክርስቶስ ካመንን በኋላ እንደፈለግን ልንኖር እንችላለን» የሚሉ ይመስላል። ስለሆነም ጳውሎስ ምንም እንኳን ደኅንነት የሥራችን ውጤት ባይሆንም፥

እግዚአብሔር እኛን ካዳነባቸው ዓላማዎች አንዱ ሕይወታችንን መለወጥ እንደሆነ ይናገራል። «ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጧልና ይህም ጸጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርን በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል»። እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ የማይመላለስ ሰው አንድም ክልቡ አላመነም። (የአእምሮ እውቀት ብቻ አለው)። ወይም ወንጌሉ ምን እንደሆነ በትክክል አልተገነዘበም ማለት ነው። ወይም ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ እየተመላለሰ በመሆኑ ለፍርድ ራሱን ያጋልጣል። ክርስቶስ እኛን ከኃጢአት በማዳኑ፥ ለንጹሕ ሕይወትና መልካምና ለማድረግም አድኖናል።

እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት ለመኖር ልንለወጥባቸው የሚገቡ አንዳንድ መንገዶች ምን ምንድን ናቸው?

1. በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በማኅበረሰብ ውስጥ መሪዎችን በመታዘዝ።
2. ሌሎችን በፍቅር በመርዳት።
3. ስለሌሎች ክፉ እንዳንናገር (እንዳንሳደብ) አንደበታችንን በመግዛት።
4. ከሌሎች ጋር በሰላም በመኖርና ለሌሎች በማሰብ።
5. የራሳችንን መንገድ ወይም የግል የክብር ከመሻት ይልቅ እግዚአብሔርን በትሕትና በማገልገል።

29፥ ጥያቄ፡– ሀ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ከሚገኙት ምእመናን አብዛኞቹ በእነዚህ አምስት መንገዶች እግዚአብሔርን ለማስከበር ቢሹ፥ በቤተ ክርስቲያንህና በማኅበረሰብህ ውስጥ ምን ዓይነት ለውጦች የሚከሰቱ ይመስልሃል? ለ) ብዙ ክርስቲያኖች በዚህ መንገድ የማይመላለሱት ለምን ይመስልሃል?

2. የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ጋር የማያባራ ሙግት መግጠም የለበትም (ቲቶ 3፡9–11)።

ሐሰተኛ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ በሚገባበት ጊዜ፥ የቤተ ክርስቲያን መሪ በቀላሉ በማያቋርጥ ክርክሮች ሊጠመድ ይችላል። ከእነዚህ ሐሰተኛ ትምህርቶች አብዛኞቹ የሞኝነት ነገሮች ሲሆኑ፥ ሌሎች ደግሞ አደገኞች ናቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪ የሞኝነት ሐሳቦችን ማራቅ ይኖርበታል። አደገኛ የሆኑትን ሐሰተኛ ትምህርቶች ግን መዋጋት አለበት። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከክርስቶስ ያገኙትን ሥልጣን በመጠቀም ሐሰተኛ ትምህርት የሚያስተምሩትንና የሚያምኑትን ሰዎች መገሠጽ አለባቸው። እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ በመሪው አሳቦች ወይም ምርጫዎች ላይ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ መመሥረት እንዳለባቸው ቀደም ብለን ተመልክተናል። ሐሰተኛ ትምህርቶችን የሚከተል የቤተ ክርስቲያን መሪ የመሪዎችን ምክር በማይሰማበት ጊዜ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቁ ተገቢ ነው። ነገር ግን የዐመጸኝነት መንፈሱ የማይፈወስ ከሆነ፥ ቤተ ክርስቲያን ግለሰቡን መቅጣት አለባት።

3. መደምደሚያ (ቲቶ 3፡12–15)

ጳውሎስ መልእክቱን ሲደመድም ለቲቶ አንዳንድ ግላዊ ትእዛዛትን ይሰጣል። ጳውሎስ አጢሞን ወይም ቲኪቆስ ቲቶን መጥተው እንደሚተኩት ይናገራል። በዚህ ጊዜ ቲቶ ወደ ኒቃፖሊስ መጥቶ ከጳውሎስ ጋር ይገናኛል። ዜማስና አጵሎስ ምናልባትም ለቲቶ የጳውሎስን መልእክት ያደረሱ ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ከዚያ በኋላ ጳውሎስ መልእክቱን በሰላምታ ይደመድማል።

30ኛ ጥያቄ፦ ከቲቶ መጽሐፍ ስለ አመራር ወይም እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ስለመመላለስ የተማርካቸውን አንዳንድ ጠቃሚ እውነቶች ዘርዝር።

አራተኛ ቀን፤ ለሳምንታዊ ስብሰባ ለመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

ሳምንታዊ ስብሰባ

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሀ) በ2ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ፥ ጳውሎስ በቅርቡ የሚፈጸምበትን የሞት ቅጣት እንዲቀበል ያስቻለው ሕይወቱ፥ ስላለፈውና ወደፊት ስለሚገጥመው ሁኔታ የሰጠው ምስክርነት ምንድን ነው? ለ) ለአንድ ሰው በሕይወቱ ፍጻሜ ላይ ስላለፈው አለመጸጸትና ወደፊት የሚጠብቀውን ደግሞ በልበ ሙሉነት መመልከት ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ክርስቲያኖች የሚያደርጓቸውና አሁን ሞተው በክርስቶስ ፊት ቢቀርቡ የሚጸጸቱባቸው የተለመዱ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) ሞትህ ከጸጸት የጸዳ እንዲሆን ቅድሚያ በምትሰጣቸው ነገሮች፥ በባሕሪህና በተግባርህ ምን ዓይነት ሰው መሆን ይኖርብሃል? ሠ) ለአንደኛ ጥያቄ በምትሰጧቸው መልሶች ላይ በጋራ ተወያዩ። 1. እያንዳንዱ ሰው ስለ አንተ በእውነት ምን ቢናገር ደስ ይልሃል? 2. በቀብር ሥነ ሥርዓትህ ላይ ሌሎች ስለ አንተ የሚናገሩአቸው ምስክርነቶች በሕይወትህ ውስጥ መገለጥ ያለባቸውን ወሳኝ ባሕርያትና ተግባራት ያሳያሉ። ሰዎች ስለ አንተ እንዲናገሩ የምትፈልገውን በትክክል ከሆንከው ጋር አነጻጽር።

2. ሀ) ጳውሎስ ጢሞቴዎስ እንዳያፍርባቸው የተናገራቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ለ) ዛሬ ሰዎች ስለ እነዚሁ ጉዳዮች የሚያፍሩት እንዴት ነው? ሐ) ብዙ ክርስቲያን እምነታቸውን ለማያምኑ ሰዎች ለማጋራት ፈቃደኛ የማይሆኑት ለምንድን ነው? መ) ሰዎች በሕይወታቸውና በምስክርነታቸው ደፋሮች እንዲሆኑ ለማገዝ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

3. ሀ) 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1–2 አንብብ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ሌሎችን እንዲያሠለጥንና እውነትን ወደ ቀጣዩ ትውልድ እንዲያስተላልፍ ምን ምን መመሪያዎችን ሰጠ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በጥንቃቄ መምረጥና ማስተማር ያለበት ለምንድን ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎችን በጥንቃቄ እያሠለጠኑ ያሉ ይመስልሃል? ካልሆነ፥ ለምን? መ) መሠረታዊ የወንጌል እውነቶችን ያስተማረህ ማን ነው? ሠ) አንተስ እነዚህን እውነቶች

ለማን እያስተማርክ ነው? ረ) ለእነዚህ የአዲሱ ትውልድ መሪዎች ምን ዓይነት እውነቶችን ማስተማር የሚያስፈልግ ይመስልሃል?

4. ሀ) ጳውሎስ የመጨረሻውን ዘመን የገለጸው እንዴት ነው? ለ) ከእነዚህ ገለጻዎች መካከል በቤተ ክርስቲያንህና በማኅበረሰብህ ውስጥ አሁን እየታዩ ያሉት የትኞቹ ናቸው? ሐ) ጳውሎስ ሐሰተኛ ትምህርት በሚኖርበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው ይላል። መ) ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪና እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዴት መመላለስ እንዳለብን በሚናገረው የእግዚአብሔር ቃል መካከል ስላለው ግንኙነት ምን አስተማረ?

5. ጳውሎስ በቲቶ መልእክት መግቢያው፥ በእውነትና መንፈሳዊነት ላይ አጽንኦት ሰጥቷል። ሀ) የእምነት ውጤት የሆኑት እነዚህ ነገሮች የአዲስ ኪዳንን መልእክት እንዴት እንደሚያጠቃልሉ ግለጽ። ለ) ከእነዚህ ከሁለቱ መካከል ቤተ ክርስቲያንህ የበለጠ አጽንኦት የምትሰጠው ለየትኛው ነው? ሐ) እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት ለመምራት እነዚህ ሁለት ቃላት አስፈላጊ የሚሆኑት ለምንድን ነው?

6. ሀ) በ1ኛ ጢሞ. 3፡1–9 እና ቲቶ ውስጥ የተገለጹትን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ባሕርያት አነጻጽር። የሚመሳሰሉት ወይም የሚለያዩት እንዴት ነው? ለ) በብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ የማይገኙት መመዘኛዎች የትኞቹ ናቸው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን የብቃት መመዘኛዎች አሟልተው መገኘታቸው ለምን ያስፈልጋል? መ) በእነዚህ የቲቶ መልእክት ውስጥ ከተገለጹት በተጨማሪ ዛሬ ትኩረት የምንሰጥባቸው ሌሎች የብቃት መመዘኛዎች የትኞቹ ናቸው? ሠ) የመሪዎች መንፈሳዊ ጥራት የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ደረጃ ሊወስን የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ።

7. ሀ) ጳውሎስ በቲቶ መልእክት ውስጥ ሰዎችን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን የገለጸው እንዴት ነው? ለ) ሽማግሌዎች ሊያሟሉ ከሚገቧቸው የብቃት መመዘኛዎች አንዱ የማስተማር ችሎታ የሆነው ለምንድን ነው? ሐ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከተመረጡት ሽማግሌዎች አብዛኞቹ ይህን የብቃት መመዘኛ የሚያሟሉ ይመስልሃል? ይህንኑ የብቃት መመዘኛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተግባራዊ እያደረጉ ነው? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪ የማስተማር ብቃት ይኖረው ዘንድ ከሚያስፈልጉት አራት ነገሮች በአንተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጎደለው የትኛው ነው? ሠ) የተሻለ የማስተማር ተግባር እንዲከናወን ምን ቢደረግ ይሻላል?

8. ሀ) ጳውሎስ አረጋውያን፥ ወጣት ሴቶች፥ ወጣት ወንዶች በሚሉ ዝርዝሮች ውስጥ ቢያንስ ሦስት ጊዜ ራስን ስለመግዛት አስፈላጊነት ይናገራል። ይህ ባሕሪ በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች አስፈላጊ የሆነው ለምን ይመስልሃል? ለ) ጳውሎስ ቲቶ መንፈሳዊነትንና ትክክለኛ ባሕሪን በሞዴልነት በማሳየት መንፈሳዊነትን እንዲያስተምር የጠየቀው ለምንድን ነው? ሐ) በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ በብዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የማይታዩት የትኞቹ ባሕርያት ናቸው? መ) እነዚህን ባሕርያት ለመልበስ ምን ሊያደርጉ ይገባል?